# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 116 ታኅሣሥ 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “ብልጽግና ለሀገርና ለሕዝብ ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብሩ ሀሳቦችን ተግባራዊ ማድረጉን አጠናክሮ ይቀጥላል”

አቶ አደም ፋራህ
-የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት



አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ብልጽግና ለሀገርና ለሕዝብ ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብሩ ሀሳቦችን ተግባራዊ ማድረጉን አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ ገለጹ።

የፌዴራል ተቋማት የብልጽግና ፓርቲ አደረጃጀት የእውቅና አሰጣጥ መርሐ ግብር ትናንት ተካሂዷል፡፡

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት አቶ አደም ፋራህ፣ ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ከሶማሌላንድ ጋር መፈራረሟ ፓርቲያችን ለሀገርና ለሕዝብ ዘላቂ መብትና ጥቅም የሚያስከብሩ ሀሳቦችን ማመንጨትና መርሕን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ያለውን አቅምና ቁርጠኝነት ያሳየበት ነው ብለዋል፡፡ ይህንኑ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ነው ያስታወቁት፡፡

ስምምነቱ ያልተገቡ መላምቶችን መና ያስቀረ፤ ብዥታዎችን የቀረፈና ያጠራ፤ እንዲሁም ኢትዮጵያ ፍላጎቶቿን የጎረቤት ሀገራትንና ሌሎች አካባቢዎችን

“ብልፅግና ለሀገርና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


## ብዝኃነትን መቀበል የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በእኩልነትና በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ብዝኃነትን መቀበል የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይ መሆኑን የባሕልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ አቶ ቀጀላ መርዳሳ ገለጹ።

“ብዝኃነትን መኖር” በሚል መሪ ቃል ከታኅሣሥ 20 እስከ 25 ቀን 2016 ዓ.ም በሀገራችን ለ14ኛ ጊዜ ሲከበር የቆየው ዓለም

ብዝኃነትን መቀበል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር)

## በዲፕሎማሲ ሳምንት

### ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኗን የሚያሳይ እንቅስቃሴ ይደረጋል

- ከጥር 2 እስከ ጥር 24 ቀን የዲፕሎማሲ ሳምንት ይካሄዳል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- በዲፕሎማሲ ሳምንት ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ተፅዕኖ ፈጣሪ መሆኗን ለማሳየት የሚያስችል የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ እንደሚደረግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ከጥር 2 እስከ ጥር

በዲፕሎማሲ ሳምንት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## በዓላትን ተከትሎ የአቅርቦት ችግር እንዳይከሰት የእርድ እንስሳት በስፋት ለገበያ እየቀረቡ ነው

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- የገናና የጥምቀት በዓላትን ተከትሎ የአቅርቦት ችግር እንዳይከሰትና የዋጋ ጭማሪ እንዳይፈጠር የተለያዩ ምርቶችን በስፋት ለገበያ የማቅረብ ሥራ እየተሠራ ነው ሲል ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

የገናና የጥምቀትን በዓል የምርት አቅርቦትን አስመልክተው ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፍሰሐ ይታገሱ፤ በዓላትን ተከትሎ የምርት የአቅርቦት ችግር እንዳይከሰትና የዋጋ ጭማሪ እንዳይፈጠር የተለያዩ ምርቶችን በስፋት ለገበያ የማቅረብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በበዓል ወቅት የሚከሰተውን የአቅርቦት ችግር ለመፍታትና የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ጠንካራ ሥራ ተሠርቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተሠራውም ሥራ በቂ ምርት ለገበያ እየቀረበ

በዓላትን ተከትሎ.. ወደ ገጽ 6 ዞሯል




AfriSky PLC ETHIOPIA
REBAR | WIREROAD | RHS | TANKER | NAIL
0940 80 80 80 | 0940 90 90 90 | 0911 21 72 55 | 0940 50 50 50

AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



አቶ ታደሰ ተስፋዬ

## ማዕከሉ ለገና በዓል የእንስሳትና እንስሳት ተዋፅዖ ምርቶችን እያቀረበ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል ለገና በዓል ከ550 ሺህ በላይ እንቁላሎችን እና ከ168 በላይ የደለቡ በሬዎችን ማዘጋጀቱን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ እንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል ሥራ አስኪያጅ አቶ ታደሰ ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ማዕከሉ ከታኅሣሥ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ ከ550 ሺህ በላይ እንቁላሎችን እና ከ168 በላይ የደለቡ በሬዎችን አዘጋጅቷል።

ማዕከሉ ለገና በዓል ከ550 ሺህ በላይ እንቁላሎችን እና ከ168 በላይ የደለቡ በሬዎችን ለከተማዋ ሸማች ዩኒየኖችና ለመንግሥት ሠራተኞች እንደሚያቀርብ የገለጹት አቶ ታደሰ፤ ማዕከሉ አሁን ላይ በቀን ከ28 ሺህ በላይ እንቁላሎችን እና ከአንድ ሺህ 300 በላይ ሊትር ወተት እያመረተ ይገኛል ብለዋል።

ማዕከሉ በዘርፉ የሚሰማሩ በ97 ማኅበራት የተደራጁ 485 የልማት ተነሺ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ከማድረግ ባሻገር የእውቀት፣ የክህሎት፣ የምርምር፣ የግብዓት፣ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ምንጭ ሆኖ እንደሚያገለግልም አቶ ታደሰ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ታደሰ ገለፃ፤ በቀጣይ የሼዶችን ቁጥር በመጨመር የነዋሪውን የኑሮ ጫና ለመቀነስ ይሠራል። በዚህም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የኑሮ ውድነትን መቋቋም እንዲችሉ እና የተመጣጠነ የአመጋገብ ሥርዓት እንዲኖራቸው እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

ማዕከሉ አንድ እንቁላል በስምንት ብር፤ ጥራቱን የጠበቀ አንድ ሊትር ወተት ደግሞ በ70 ብር እየሸጠ ይገኛል። የኑሮ ውድነትን በማረጋጋት ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ የላቀ አስተዋፅዖ እያበረከተ ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ ይህም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች የተመጣጠነ ምግብ ለማግኘት በጀት መመደብ እንዲጀምሩ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

የኑሮ ውድነት ያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ በከተማ አስተዳደሩ ትኩረት እንዲሰጠው በማድረጉ የእንስሳት ልማትና ልህቀት ማዕከል ተገንብቷል። ማዕከሉ እንቁላልና ወተት ለነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ በመሆኑ ፕሮቲን ያላቸውን ምግቦች ማግኘት ተችሏል። ይህም ከግለሰብ ባለፈ ጤናማ ማኅበረሰብ እንዲኖር ያደርጋል ነው ያሉት አቶ ታደሰ።

ማዕከሉ 10 የወተት ላም ሼዶች፣ 10 የዳልጋ ከብት ማደለቢያ ሼዶች፣ 11 የእንቁላል ጣይ ዶሮ ሼዶች፣ 32 የምርት ማሳያ እና መሸጫ ሱቆች፣ ዘመናዊ የእንስሳት ክሊኒክ፣ ዘመናዊ የእንስሳት ላብራቶሪ እና ሁለት የመኖ ማቀነባበሪያ በውስጡ ይዟል።

# በሕገወጥ መንገድ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች በአንድ ወር ውስጥ ሕጋዊ ሰነድ ሲይዙ ይገባል

### - ከ18 ሺህ በላይ ዜጎች ሐሰተኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ይዘው ተገኝተዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሕገወጥ መንገድ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሕጋዊ ሰነድ ሊይዙ እንደሚገባ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት አስታወቀ። በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከ18 ሺህ በላይ ዜጎች ሐሰተኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ይዘው ተገኝተዋል።

የኢሚግሬሽንና የዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሠላማዊት ዳዊት ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች ሐሰተኛ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ሐሰተኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ሕገወጥ ፓስፖርትና ቪዛ፣ ሐሰተኛ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያና ሐሰተኛ ሰነድ አዘጋጅተው በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እየኖሩ እንደሚገኝ ተረጋግጧል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ዜጎች የመኖራቸውን ያህል በሐሰተኛ ሰነዶች የሚኖሩ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች በመኖራቸው ጉዳዩን ማጥራት ይገባል ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ በተደረገው የማጣራት ሥራ ከ18 ሺህ በላይ ሰዎች ሐሰተኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ ይዘው መገኘታቸው ተረጋግጧል ብለዋል።

ከአንድ ሺህ 500 በላይ ሐሰተኛ ቪዛ እና ከአንድ ሺህ 800 በላይ ሕገወጥ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ የያዙ ዜጎች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች መገኘታቸውንም አመላክተዋል።




ሠላማዊት ዳዊት

የኢሚግሬሽን ሥርዓትን ሳያሟሉና በሕገወጥ መንገድ ወደ ሀገር ገብተው እየኖሩ ያሉ፤ ቪዛና የመኖሪያ ፈቃዳቸውን ሳያሳድሱ ከተፈቀደላቸው የጊዜ ቆይታ በላይ የሚቆዩ እንዲሁም የካምፓኒ ምዝገባ ሳያደርጉ የውጭ ሀገር ዜጎችን በማሠራት ላይ ያሉ ተቋማት መኖራቸውንም አስረድተዋል።

በሕገ ወጥ መንገድ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈው የሚሰጡ በመሆናቸው ክትትሉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ዋና ዳይሬክተሯ ገልጸዋል።


እነዚህንና ሌሎች ሕገወጥ ሰነድ ያላቸው ዜጎች ከጥር 1 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ወደተቋሙ በመምጣት ሕጋዊ ሰነድ እንዲዘጋጅላቸው የሚረዳ መረጃ መስጠት እንዳለባቸው አመላክተዋል።

በሕገወጥ መልኩ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዜጎች በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሕጋዊ ሰነድ እንዲዘጋጅላቸው ካላደረጉ መንግስት አስፈላጊውን ርምጃ እንደሚወሰድ አሳስበዋል።

በተለያየ ምክንያት ሕጋዊ ሰነድ የሌላቸውን ዜጎች ለማጣራት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ሕጋዊ ሰነድ በማያሟሉ ሰዎች ላይ ርምጃ የመውሰዱ ተግባርም ከፌደራል ፖሊስና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጥምረት እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

ብልሹ አሠራሮችን መፍታት የሚቻለው ቴክኖሎጂን መጠቀምና አሠራርን ማዘመን ሲቻል ነው ያሉት ወይዘሮ ሰላማዊት፤ የተለያዩ ሰዎችንና ኩባንያዎችን መረጃ ለመመዝገብ እንዲሁም በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ለማጣራት እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ዜጎች እየተጠቀሙበት የሚገኘውን ፓስፖርት ኤሌክትሮኒክ (ኢ-ፓስፖርት) ለማድረግ እና ለማዘመን እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።



# "ገናን በላሊበላ ለማክበር የሚመጡ እንግዶችን በአግባቡ ለማስተናገድ ዝግጁ ነን"

### - አባ ሕርያቆስ ፀጋዬ
### የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ዋና አስተዳዳሪ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ገናን በላሊበላ ለማክበር ለሚመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ ዝግጁ ነን ሲሉ የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ዋና አስተዳዳሪ አባ ሕርያቆስ ፀጋዬ ገለጹ፡፡

የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ዋና አስተዳዳሪ አባ ሕርያቆስ ፀጋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የገናን በዓል ለማክበር ወደ አካባቢው ለሚመጡ እንግዶች ኢትዮጵያዊነትን በተላበሰ የእንግዳ አቀባበል ለማስተናገድ የሚያስችል ዝግጅት ተደርጓል፡፡

ከተለያዩ አካባቢዎች የተነሱ እንግዶች ወደከተማው እየገቡ መሆኑን የጠቆሙት አባ ሕርያቆስ፤ ወደ ስፍራው የሚመጡ እንግዶችን ተቀብሎ ማረፊያ በመስጠት እና እግር በማጠብ ቅድሚያ አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው፡፡

ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን እንዲከታተሉና ጉብኝት እንዲያደርጉ ለማገዝም አስፈላጊው ዝግጅት ተከናውኗል ብለዋል።

በተቋቋመው ዐቢይ ኮሚቴ አማካኝነት ለክብረ በዓሉ የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ጠቅሰው፤ የገና በዓል ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ በውቅር አብያተ ክርስቲያናቱ ይከናወናል ሲሉ ተናግረዋል።

ቀደም ሲል በገና ክብረ በዓል ከውጪና ከሀገር ውስጥ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ታዳሚዎች እንደሚገኙ ያስታወሱት አስተዳዳሪው፤ በዘንድሮው በዓል እንደቀድሞው ባይገኙም እስከ አንድ ሚሊዮን ሰዎች በበዓሉ ይታደማሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በበዓሉ ዕለት የሚካሄደው "ቤዛ ኩሉ" የተሰኘው የምስጋና ሥርዓት ለበዓሉ ትልቅ ድምቀት መሆኑን ጠቁመው፤ የቅዱስ ላሊበላ ሊቃውንት ምስጋናውን ከሚስብ መንፈሳዊ ትርዒት ጋር እንደሚያቀርቡ አስረድተዋል።

በቅዱስ ላሊበላ የሚከናወነውን ትዕይንት ልዩ የሚያደርገው ቤተ-ማርያም በተሰኘው የቤተልሔም ምሳሌ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ሊቃውንት ተሰባስበው ወረብና ምስጋና የሚያቀርቡበት በመሆኑ ነው ያሉት አስተዳዳሪው፤ ይህን ትዕይንትም ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ጭምር የሚታደሙበት በመሆኑ በልዩ ሁኔታ ይቀርባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በየዓመቱ በርካታ ኢትዮጵያውያን የእምነቱ ተከታዮች፣ የውጪ ሀገራት ዜጎች የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት በዓል በቅዱስ ላሊበላ ተገኝተው እንደሚያከብሩ ገልጸው፤ የአካባቢው ነዋሪዎችም እንግዶች የሚያርፉባቸውን ቦታዎች በማዘጋጀትና አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ የሚያስተናግዱ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ቦታው ከእምነቱ ተከታዮች ባሻገር ለበርካታ ጎብኚዎች ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ልዕልና የሚሳይ ድንቅ ኪነ-ሕንፃ ያረፈበት መሆኑን ጠቅሰው፤ የእምነቱ ተከታይ ምዕመናን በረከት የሚያገኙበት፣ ከሌላ ወገን ያሉት ዜጎች ቀደምት አባቶቹ የሠሩትን ድንቅ ሥራ አይተው የሚያደንቁበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል በድምቀት ከሚከበርባቸው ሃይማኖታዊ ስፍራዎች መካከል የደብረ ሮሐ ቅዱስ ላሊበላ ዋነኛው ነው።

## “ሃይማኖታዊ በዓላት የመንፈሳዊ ልዕልና መገለጫ መድረኮች በመሆናቸው ፖለቲካዊ መልዕክቶች ሊተላለፍባቸው አይገባም”

### - የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትና ስብስቦች የመንፈሳዊ ልዕልና መገለጫ መድረኮች በመሆናቸው ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው መልዕክቶች ሊተላለፍባቸው እንደማይገባ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ አስታወቀ።

ጉባኤው ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳለው፤ ሃይማኖቶች የመንፈሳዊ እና ማኅበራዊ ዕሴት መሠረቶች በመሆን ከፍተኛ የሆነ የሥነ ምግባርና የግብረ ገብነት ትምህርትና ግንባታ የሚከናወንባቸው ማዕከላት ናቸው። በመሆኑም ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትና ስብስቦች የመንፈሳዊ ልዕልና መገለጫ መድረኮች በመሆናቸው ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው መልዕክቶች ሊተላለፍባቸው አይገባም።

እንደ ጉባኤው መግለጫ፤ ሃይማኖታዊ ትዕዛዛትና አስተምህሮዎች የሰዎች ማኅበራዊ ግንኙነትና ቁርኝነትን በማጠናከር ሠላም፣ መከባበር፣ አብሮነት፣ ይቅርታ፣ እርቅ፣ ፍትሕ እና የመሳሰሉ በጎ ዕሴቶችን በማስተማር ዘመናትን የዘለቀ አገልግሎት ሲሠጡ ኖረዋል፤ እየሠጡም ይገኛሉ። ይህም ሀገራዊ አንድነትን አስጠብቆ ለመዝለቅ አስችሏል።

ከዚህም ባለፈ የሃይማኖት አባቶች ዋና ተልዕኳቸውና አገልግሎታቸው የሰው ሁለንተናን ማገልገልና አማኞች ፈሪሀ ፈጣሪ አድሮባቸው የመንፈሳዊ ልዕልና እንዲጎናፀፉ ማድረግ መሆኑን ያነሳው መግለጫው፤ ለዚህም ራሳቸውን ከዓለማዊ ጉዳዮችና ጣጣዎች በማራቅ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት በምሳሌነት እየኖሩ አስተምህሮው የሚያዛቸውን በተግባር ገልጠዋል ብሏል።

የሰዎች ማኅበራዊ ግንኙነትና መስተጋብርም የሰመረ እንዲሆን መንፈሳዊ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በማስተማር፣ በመምከርና በመገሰፅ የአባትነት፣ የጠባቂነትና የመሪነት አደራቸውንና ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፤ እየተወጡም ይገኛሉ ሲል አትቷል።

በመንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚስተዋሉ በደሎችንና ኢ-ፍትሐዊነቶች ሁሉ እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ መጣር፤ አጥፊዎችም ከስህተታቸው እንዲታረሙ በፍቅር መገሰፅ ሃይማኖታዊና የተለመደ አሠራር በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ጉባኤው በመግለጫው አመላክቷል።

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች ከዚህ መሠረታዊ ተልዕኮና ዓላማ በማይስማማ አኳኋን ለሃይማኖታዊ ተግባርና ዓላማ በሚደረጉ ስብስቦች እና በተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያ በኩል ተገቢ ያልሆኑ መልዕክቶችን ሲያስተላልፉ መስተዋሉን የጉባኤው መግለጫ አመላክቷል።

ሲተላለፉ የተስተዋሉት መልዕክቶች በአብዛኛው ፖለቲካዊ ይዘት የጎላባቸው፣ ሀገር አፍራሽና ደም አፋሳሽ ስብከቶችና ትንታኔዎች መሆናቸውን መግለጫው አብራርቷል።

ስብከቶቹና ንግግሮቹ ፖለቲካውና ፖለቲከኞችን የሚተቹ ወይም የሚደግፉ ከመሆናቸው በላይ አንዱ በአንዱ ላይ እንዲነሳ የመቀስቀስና የማነሳሳት አዝማሚያ የሚታይባቸው መሆናቸውን ጠቅሶ፤ ጉዳዩ ከየትኛውም ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ጋር የማይስማማና ድጋፍም የሌለው መሆኑ ደግሞ የስብከት ልምምዱ አደገኛና በእጅጉ የሚወገዝ ነው ብሏል።

በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ ስብከትና አካሄድም የሠላም፣ የመከባበርና የአብሮነት ዕሴቱን የሚጎዳ በመሆኑ በአፋጣኝ ሊታረም እንደሚገባ ጠቁሞ፤ የሃይማኖት ተቋማትም እንዲህ ዓይነት ስብከት የሚሰብኩና የሚናገሩ አባቶችን፣ አስተማሪዎችን ወይም ሰባኪ አገልጋዮችን እንዲታረሙ በማድረግ ተቋማዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ጉባኤው አሳስቧል።

# ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ባሕላቸውን እንዲያውቁ የሚያደርጉ ዝግጅቶች ተሰናድተዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ወደ ሀገራቸው የሚመጡ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ባሕላቸውን እንዲያውቁ የሚያደርጉ ዝግጅቶች የተሰናዱ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሪት ሌንሳ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ደርጅት እንደገለጹት፤ በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባደረጉት ጥሪ መሠረት ወደ ሀገራቸው የሚመጡ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሚኖራቸውን ቆይታ ባሕሎቻቸውን እና እሴቶቻቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ ወጣቶችን መሠረት ያደረጉ ዝግጅቶች ተሰናድተዋል፡፡

ወይዘሪት ሌንሳ እንዳሉት፤ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያኑ በሁሉም አካባቢዎች ተንቀሳቅሰው እንዲጎበኙ ከማድረግ ባሻገር ባሕላቸውን በቅርበት እንዲያዩ የሚያስችላቸው የፌስቲቫል ይዘት ያላቸው ሁነቶች ይካሄዳሉ፡፡

በተጨማሪም ወጣቶች እርስ በእርሳቸው የሚገናኙበት መድረኮች እንደሚኖሩ ተናግረዋል፡፡

ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያኑ ሀገራቸውን በሚገባ እንዲያውቁ የሚያግዙ ሥራዎችን እንዲሠሩ ከአገልግሎት ሰጪዎችና ከመገናኛ ብዙኃን በጋራ መሥራት መጀመሩን ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል፡፡

ሁለተኛ ትውልዶቹ በኢትዮጵያ የሚኖራቸው ቆይታ ባሕላቸውን የሚያውቁበት እና ከመረጃ ባሻገር ያለውን እውነት አይተው የሚረዱበት እንደሚሆንም ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የተገነቡት እና በግንባታ ላይ ያሉት ትልልቅ የቱሪዝም ፕሮጀክቶች የቱሪዝሙን ዘርፍ በማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከቱ መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሚኖራቸው ቆይታ በሚያዩት ነገር ተደስተው እንደሚሄዱ እምነታቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንደ ሀገር የቱሪዝሙን ዘርፍ ለማሳደግ እየተሠሩ ያሉት ሥራዎች እጅግ አበረታች መሆናቸውን ገልጸው፤ በቅርቡ ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት የሆነው የጨበራ ጩርጩራ ዝሆን ዳና ሎጅ ትልልቅ እንግዶችን ለማሳረፍ የራሱ አስተዋፅዖ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ በርካታ የማስተዋወቅ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረው፤ ለጉብኝት የሚመጡት ቱሪስቶች



ወይዘሪት ሌንሳ መኮንን

ምቹ ማረፊያና መዝናኛ ቦታ ሲያገኙ ተመላልሰው የመምጣት እና የመጎብኘት ፍላጎታቸው እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ የማስተዋወቅ ሥራ ሲሠራ በቂ እና ምቹ የማረፊያ ስፍራ በማዘጋጀት እንዲሁም የሚጎበኙ ቦታዎችን ምቹ በማድረግ መሆን አለበት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በዚህ ረገድ ቱሪዝም ላይ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡

የውጭ ሀገር ቱሪስቶች መጥተው ሀገራቸውን እንዲጎበኙ የዲጂታሉን አማራጭ በመጠቀም የማስተዋወቅ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ያወሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ የተደረገላቸው በውጭ ሀገር የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልዶችም መጥተው ሀገራቸውን እንዲያውቁና እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# በመዲናዋ የገናና የጥምቀት በዓላት በሠላም እንዲከበሩ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የመዲናዋ ነዋሪዎች የገና የጥምቀትን በዓል በሠላም እንዲያከብሩ የሚያስችል ዝግጅት ተደርጎ ወደ ተግባር ተገብቷል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሠላምና ፀጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ጌታሁን አበራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመዲናዋ ነዋሪዎች የገና እና የጥምቀትን በዓላትን በሠላም እንዲያከብሩ የሚያስችል ዝግጅት ተደርጎ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በዓላቱ ተጀምረው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የሠላም ሠራዊቱ ከፀጥታ አካላትና ከማኅበረሰቡ ጋር በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን አቶ ጌታሁን ተናግረዋል፡፡

በዓላትን ማኅበረሰቡ ያለምንም የፀጥታ ስጋት እንዲያከብር እቅድ በማቀድ ወደ ተግባር ተገብቷል ያሉት ኃላፊው፤ በሠላም ተከብረው እንዲጠናቀቁ የሚያስችል ስምሪት መሰጠቱንም አብራርተዋል፡፡

በዓላትን ሽፋን በማድረግ በሕገ ወጥ መንገድ የግብይት ሥርዓቱን የሚያውኩ አካላት እንዳይኖሩና ገበያውን የሚረብሹ አሠራሮች እንዳይፈጠሩ በማድረግ የግብይት ሥርዓቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲከናወን ፀጥታን የማስከበር ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡



አቶ ጌታሁን አበራ

በተጨማሪም የግብይት ሥርዓቱን ዋጋ በመጨመር የሚያውኩ፤ ምርት የሚከዝኑ፤ በምርቶች ላይ ባዕድ ነገር በመቀላቀል ለማኅበረሰቡ የሚያቀርቡ እና ሐሰተኛ የብር ኖት እያተሙ በገበያ የሚያሰራጩ አካላትን የመለየትና አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ የመውሰድ ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

የመዲናዋ ነዋሪ የገና እና የጥምቀትን በዓል በሰላም እንዲያከብር በአምስቱም መግቢያና መውጫ ኬላዎች ላይ አስፈላጊውን ቁጥጥርና ክትትል የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰውም፤ እየተሠራ ያለው ሥራ በዓላትን ሽፋን በማድረግ በሕገ ወጥ መንገድ የሚገቡ ምርቶችንና የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን ለመከላከል የሚያስችል ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ኅብረተሰቡ በዓላትን ምክንያት በማድረግ የሚገበይባቸውን የገበያ ማዕከላት፤ ባዛሮችና የእሁድ ገበያዎች ተገቢውን ሕግ የማስከበር ሥራ በመሥራት ኅብረተሰቡ በተረጋጋና በሰላማዊ መንገድ እንዲገበያይ የማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የጥምቀት በዓል የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የዓለም በዓል ነው ያሉት አቶ ጌታሁን፤ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችና ሚዲያዎች በዓሉን ለማክበር የሚመጡ መሆኑን ጠቅሰው በዓሉን በሠላም አክብረው እንዲመለሱ ፀጥታን የማስከብር ሥራ ለመሥራት ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል፡፡

የጥምቀትን በዓል በሠላም ተከብሮ እንዲያልፍ ከፀጥታ አካላትና ከማኅበረሰቡ ጋር በቅንጅት ይሠራል ሲሉ አመላክተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከሀገር ጥቅም በተጻራሪ መቆም ነውር ነው!

በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኝ ሀገር ዜጋ ደረጃው ይለያይ እንጂ ስለ ሀገሩና ሕዝቡ የሚቆረቆር ማንነት አለው። ይህ ማንነቱ በደግ ቀናት ለሀገሩ በጎ ከማሰብ ጀምሮ በክፉ ቀን ውድ የሆነውን ሕይወቱን እስከ መስጠት የሚደርስ ነው። ይህ እውነታ ሀገራት እንደሀገር እንዲቀጥሉ ከማስቻል ባለፈ፤ የሀገርና የሕዝብን ጥቅም በማስከበር ሂደት ውስጥ ወሳኝ አቅም እንደሆነ ይታመናል።

በተለይም አሁን ባለንበት ወቅት፤ ዓለም በብዙ ፍላጎቶች እና እነዚህን ፍላጎቶች ለማስፈጸም የሴራ ፖለቲካ እንደ አንድ አማራጭ ስትራቴጂ እየተወሰደ ባለበት ሁኔታ፤ ሀገር እንደ ሀገር እንድትቀጥም ሆነ፤ የሀገርና የሕዝብ ጥቅሞች ተጠብቀው እንዲቀጥሉ ዜጎች፤ ዓለም አቀፋዊ እውነታውን ተረድተው ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለሀገራቸው ዘብ ሊቆሙ ይገባል።

በተለይም ወቅታዊ የፖለቲካ ሞቅታዎች ሊፈጥሩ ከሚችለው መጠለፍ፤ ዓለም አቀፍ ሴራዎች ሊያመጡ ከሚችሉት የመለያየት አደጋዎች፤ በማንነት ላይ ከተገነባ የእልህ ፖለቲካ ራሳቸውን በማቀብ እንደዚህ አይነት አስቸጋሪ ወቅቶችን በተረጋጋ መንገድና በሰከነ መንፈስ ማሳለፍ የሚያችል ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅባቸዋል ።

ይህን አይነት ዝግጁነት ማጣት የሀገርና ሕዝብን ተጠቃሚነት አደጋ ውስጥ የሚከት፤ ሀገርን እንደ ሀገር ሊያሳጣ እንደሚችል ከዓረብ የፀደይ አብዮት ማግስት በመካከለኛው ምስራቅ የሆነውን ተጨባጭ እውነታ ማስታወስ ተገቢ ነው። ወቅቱ የፈጠረው ሞቅታ፣ የእልህ ፖለቲካ እና ዓለም አቀፍ ሴራ ተዳምረው የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ ባለቤት የሆኑ ሀገራትን ሳይቀር መንግሥት አልባ በማድረግ ሕዝቦቻቸውን ለሞት፣ ለስቃይና ለስደት ዳርጓል ።

እኛ ኢትዮጵያውን ካለን የዘመናት የሀገረ መንግሥት ምስረታ ታሪክ አንጻር በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ የመጣን፤ ዛሬም በብዙ ውጣ ውረዶች እየተፈተን ያለን ሕዝቦች ነው። ይህ እንደ ሕዝብ ትውልዶች እያለፉበት ያለው የፈተና ሕይወት በብዙ መልኩ ስለሀገራችን የበለጠ ቀናኢ እንድንሆን፤ በሀገር ጉዳይ አንድ ዓይነት ድምፅ እንዲኖረን፤ ከሀገርና ከሕዝብ የምናስቀድመው ነገር እንዳይኖረንም ትልቅ አቅም ሆኖናል ።

ከዚህ የተነሳም ጠላቶቻችን በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሀገር ተከፋፍለዋል፤ በመካከላቸው ያለው መከፋፈል ለዓላማችን ስኬት ጉልበት ይሆነናል ብለው፤ ለከንቱ ዓላማቸው ሊያንበረክኩን በተንቀሳቀሱባቸው ወቅቶች ሁሉ ባልጠበቁት እና ባልገመቱት መንገድ የልዩነት አጀንዳዎቻችን ጥለን ስለሀገራችን በአንድነት ተሰልፈን፤ በብዙ የተጋድሎ መስዋዕትነት ሀገራችንን አስጠብቀን ቆይተናል ።

የብሔራዊ ማንነታችን አንድ አካል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ሀገራዊ ትርክታችን አንድ ምዕራፍ እና ልዩ ቀለም የሆነው መገለጫችን፤ ከትውልድ ትውል እየተላለፈ ለመጣው፤ እንደ ሕዝብ የነፃነት ቀንዲል ሆነን እንድናበራ ያስቻለን ይሄው ስለሀገርና ስለ ሕዝብ ያለን የጸና ወገንተኝነት፤ ነገም ተስፋ ለምናደርጋት የበለጸገች ሀገር ግንባታ መተኪያ የሌለው አቅማችን እንደሚሆን ይታመናል።

ይህም ሆኖ ግን አሁን አሁን ከዚህ ብሔራዊ ማንነታችን ተምጠው ያልተወለዱ፤ ከሀገርና ከሕዝብ ተጠቃሚነት ባፈነገጠ መልኩ ጊዜያዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት፤ የፖለቲካ መሻታቸውን እውን ለማድረግ፣ ከዚያም አልፈው በግልጽ በባንዳነት የጠላቶቻችን መሣሪያ በመሆን ሌት ተቀን ያለ እንቅልፍ የሚዳክሩ "ኢትዮጵያውያንን" ማየት እየተለመደ መጥቷል።

ይህ እውነታ በተለይም ባለፉት ሦስት ዓመታት፣ እንደ ሀገር በመጣንባቸው ውጣ ውረዶች ውስጥ በተጨባጭ ተስተውሏል። በእነዚህ ዓመታት እንደሀገር ለከፈልናቸው ያልተገቡ ዋጋዎችም ተጠቃሽ ነው። በጉዳዩ ዙሪያ ሕዝባችን ተገቢውን ግንዛቤ መጨበጥ ካልቻለ ተስፋ ያደረግናቸውን ነገሮች ሊያጨልምብን እንደሚችልም መገመት አይከብድም።

የሀገር ዋጋ፣ የሀገር ፍቅር፣ የሕዝብ ጥቅምና ለሕዝብ ጥቅም የሚከፈል ዋጋ ምንነት በአግባቡ ያልተረዱ፤ ለመረዳትም ፈቃደኛ ያልሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች፤ አሁን አሁን ፍጹም በሆነ ጠላትነት፤ በአደባባይ ከሀገርና ከሕዝብ ጥቅሞች በተጻራሪ ያለ እፍረት፣ ቆመው ማየት፤ ሲጮሁ መስማት የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ሆኗል ።

እነዚህ ግለሰቦች ሀገር ከጊዜያዊ ፍላጎታቸው እና ከፖለቲካ መሻታቸውን በላይ መሆኗን፣ በብዙ ትውልዶች የመስዋዕትነት ቅብብሎሽ እዚህ መድረሷን፤ ከነሱ በፊት የነበረች፣ ከነሱ በኋላ የምትኖር፤ የልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው የተስፋ አድማስ እንደሆነች አሳዛኝም አሳፋሪም ነው።

ይህ ተግባራቸው የቀደሙት አባቶቻችንን ስለ ሀገርና የሕዝብ ጥቅም ብዙ ዋጋ ከፍለው የጻፉትን ደማቅ ታሪክ የሚያደበዝዝ ፤ እንደ ትውልድ የሁላችንንም አንገት የሚስደፋ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለዘመናት የምንታወቅበትን ብሄራዊ ማንነታችንን የሚያሳንስ፤ በሀገርና በሕዝብ ጥቅም ላይ የሚቀነቀን አሳፋሪና ነውረኛ ተግባር ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የዓውደ ዓመት ገበያው በዓሉን እንዳያደበዝዝ

መልካምሥራ አፈወርቅ

ኢትዮጵያውያንና ነባር ባሕላዊ እሴቶቻቸውን ነጣጥሎ ማየት አይሞከርም። ለዘመናት አብሯቸው የኖረው ማንነት ከሃይማኖት፣ ባሕልና ዕምነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ይህ እውነታ እነዚህን ሕዝቦች ከነደማቅ ቀለሞቻቸው ሳይፈዙ፣ ሳይበረዙ እንዲኖሩ አስችሏቸዋል።

ከኢትዮጵያውያን የማንነት መገለጫዎች አንዱ ከሃይማኖትና ባሕል ጋር ተያይዞ የሚያከብሯቸው ዓውደ ዓመቶች ዋንኞቹ ናቸው። እነዚህ ጊዜና ወቅትን ጠብቀው በድምቀት የሚከበሩ በዓላት ከጥንት እስከ ዛሬ በየትውልዱ ዓውድ ሲሸጋገሩ ዘመናትን ቆጥረዋል።

ዓውደ ዓመት ማለት ለኢትዮጵያውያን ትርጉሙ ብዙ ነው። ጊዜያትን ጠብቀው ቢፈራረቁም ቀኑ ላይ በዋሉ አጋጣሚ ሁሉ እንደ አዲስ ሆነው ይከበራሉ። ዓውደ ዓመት ለአክባሪው ሁሌም ድንቅና ብርቅ ነው። ዕለቱን ተከትሎ የሚኖረው ማኅበራዊነት አብሮ የመኖር ስንቅ ሆኖ ይዘልቃል ።

> **ዓውደ ዓመት ማለት ለኢትዮጵያውያን ትርጉሙ ብዙ ነው። ጊዜያትን ጠብቀው ቢፈራረቁም ቀኑ ላይ በዋሉ አጋጣሚ ሁሉ እንደ አዲስ ሆነው ይከበራሉ። ዓውደ ዓመት ለአክባሪው ሁሌም ድንቅና ብርቅ ነው። ዕለቱን ተከትሎ የሚኖረው ማኅበራዊነት አብሮ የመኖር ስንቅ ሆኖ ይዘልቃል**

ይህ ቀን ለአብዛኞች ውስጠት ደስታን ያጎናጽፋል። ይህ ጠንካራ የማንነት ገመድ በእያንዳንዱ ጎጆና ቤተሰብ አይቀሬ ውዴታ ነው። ከዚህ አለፍ ሲል ጎረቤትና ዘመድ አዝማድን በአንድ የማዋል፣ አብሮነትን በስፋት የማጠናከር ኃይል አለው።

ማንም እንደሚያውቀው ለዓውደ ዓመት የሚሰጠው ግምት ከፍ ያለ ነው። በዚህ ቀን ሁሉም እንደቤቱ ዕለቱን በድምቀት ያከብራል። የእጁን ከፍሎ የአቅሙን አጋርቶ ከሌሎች መስሎ ተመሳስሎ ይውላል። ይህ ይሆን ዘንድ ከጥንት እስከዛሬ ያልተሸረሸው ተለምዷዊ እሴት ውዴታዊ ግዴታን እንደጣለ ቀጥሏል።

ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ በሀገራችን እየተስተዋለ ያለው ከፍተኛ የኑሮ ውድነት የነዋሪውን አቅም እየፈተነው ይገኛል። ዛሬ ገንዘብ ይሉትን ይዞ ገበያ የወጣ ሸማች የልቡን ሳያደርስ፣ ያሰበውን ሳያሳካ ከቤቱ መመለሱ ብርቅ አልሆነም። በአሁኑ ጊዜ በእያንዳንዱ ሸቀጥ ላይ በየአፍታው የሚጨመረው ዋጋ የኅብረተሰቡን የመግዛት አቅም ከፈተና በላይ አድርጎታል።

ዛሬን እየናረ ላለው የኑሮ ውድነት በእሳት ላይ ጋዝ የሚጨምሩ፣ ከብዙኃኑ ጥቅም ለግል ዓላማቸው የሚሮጡ ራስ ወዳዶች ተበራክተዋል። ‹‹እንኳን ዘንቦልሽ›› እንዲሉ ሆኖም ምክንያትና አጋጣሚን የሚሹ አንዳንድ ነጋዴዎች የዓውደ ዓመትን የመሰሉ ሰበቦች ሁሌም ሠርግና ምላሻቸው ነው።

በእነዚህ ስግብግቦች ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ ችግሮች መፍትሔ የላቸውም። ተደጋግሞ እንደሚስተዋለው አጋጣሚን የሚሹ አንዳንድ ነጋዴዎቹ እንደ ሁልግዜው ልምዳቸው መጋዘኖቻቸውን በሸቀጦች ሞልተው የራሳቸውን ጊዜ ይጠብቃሉ። ቀድመው በአነስተኛ ዋጋ ያስገቧቸውን ዕቃዎችም ዓውደዓመቱ ሲቃረብ ከእጥፍ በላይ አትርፎ ለመሸጥ አይደራደሩም።

ይህ አይነቱ ተለምዷዊ አሠራር እስከዛሬ ብዙኃኑን ላልተገባ ወጪ ዳርጎ፣ የጥቂቶችን ኪስ ሲያዳጉስ ቆይቷል። ዛሬም ቢሆን ሽቅብ በናረው የኑሮ ውድነት ላይ ተጨማሪ ችግር የሚያክሉ ራስ ወዳዶች ጥቂት አይደሉም። አሁንም መጋዘን የሚያሰፉ፣ ዛሬም ለትርፍ የሚሮጡ በርካቶች ናቸው።

ይህን ችግር ተከትሎ ከጥቂት ጊዜያት በፊት ከመንግሥት በተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች በከተማዋ በተመረጡ አካባቢዎች የዕሁድ ገበያዎች ተደራጅተዋል። እነዚህ የገበያ ስፍራዎች ለሸማቹ የሚያስፈልጉ የምግብ ሸቀጦችን ከመደበኛው የገበያ ዋጋ በተሻለ እንዲያቀርቡ ሲባል የተዘጋጁ ናቸው።

ከእነዚህ አቅራቢዎች አብዛኞቹ ሥራ በጀመሩ ሰሞን የተቋቋሙበትን ዓላማ በአግባቡ ሲተገብሩ ቆይተዋል። ይህን በማድረጋቸውም በተመጣጣኝ ዋጋ ፍላጎቱን ለሚሞላው ተጠቃሚ መድሕን መሆናቸው ይታወሳል። ዋል አደር ሲል ግን ጥቂት የማይባሉት ታማኝነታቸው ተሸርሽሮ፣ ለትርፍ ብቻ ሲሯሯጡ ተስተውለዋል ።

አንዳንዴ በነዚህ የገበያ ስፍራዎች ከሌሎች ነጋዴዎች ባልተሻለ መልኩ ግብይት ይካሄዳል። አንዳንዶች የተቀበሉትን አደራ ዘንግተው ሸቀጦችን በእጥፍ ዋጋ ይሸጣሉ። በነዚህ ስፍራዎች የሚገኙ አቅራቢዎችን እንዴትና ለምን ብሎ መጠየቅ ነውር እስኪመስልም መከራከር አይቻልም። በዚህ መሐል ኪሱ የሚራቆተው፣ ኢኮኖሚው የሚሳሳው ሸማች ጉዳቱ ቀላል አይሆንም።

ተደጋግሞ እንደሚስተዋለው የኑሮ ውድነት መልኩ ደምቆ የሚጎላው በበዓላት ግብይት ወቅት ነው። በአንድም ይሁን በሌላ ገበያውን መርገጥ ግድ የሚለው ሸማች በዚህ ወቅት አስተውሎ ካልገበየ በስግብግቦች እጅ የመውደቁ ዕድል ሰፊ ይሆናል።

ብዙ ግዜ ለኑሮ ውድነቱ መባባስ ምክንያት ሆነው የሚጠቀሱ ማሳያዎች ይኖራሉ። በጦርነት ሳቢያ በሀገር ላይ ሠላምና አለመረጋጋት መኖር፣ በምርት ላይ የሚያጋጥም ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ አደጋዎች፣ በወቅቱ ምርት ያለመሰብሰብና መሰል ምክንያቶችን በዝርዝር ማስቀመጥ ይቻላል።

ምንግዜም በተጠና የገበያ ስልት ዓውደ ዓመቱን ተከልለው ትርፍ የሚያጋብሱ አንዳንዶች ግን የሸማቹን አቅም ለማዳከም ወደኋላ የሚሉ አይደሉም። ምርት ሳይጠፋ፣ ግብዓት ሳይጎድል በወቅቱ ላይ የሚንጠላጠሉ አትራፊዎች ከራሳቸው ጥቅም የዘለለ የሌላውን ችግርና ጎዶሎ የሚያዩበት ዓይን ኖሯቸው አያውቅም።

እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ በሰፋ ጊዜ ግን ቀዳሚው የመፍትሔ ትግል ከራስ ሊጀምር ግድ ይላል። ዓውደ ዓመት በደረሰ ጊዜ ከኑሮ አጉድሎ፣ ከራስ ቆርሶ ተበድሮ የሚደረግ ልማዳዊ ጉዞ ለማንም አይበጅም። ይህ አይነቱ ተሞክሮ የሚቀጥል ከሆነም በአጭር ሊቀጭና ሊቋጭ ያስፈልጋል። ለምን ከተባለ ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይኖርምና ።

አቅምን አውቆና ለክቶ፣ ከራስ ጓዳ ተማክሮ የሚውሉበት ገበያ ቢጠቅም እንጂ አይጎዳም። ትናንት በነበረ የገበያ ዋጋ ዛሬን አስቦ መግዛት እንደማይቻልም ነጋሪ አያሻም። አስቀድሞ ስለነገ ሕይወቱ አርቆ የሚያስብ ቢኖር እርሱ ብልህና አዋቂ ነው። ምንግዜም ይህን ያደረገ ራሱን ከችግር ያተርፋል። ነገን ያለሀሳብ ይሻገራልና ።

ዓውደ ዓመቱን አሳበው ዋጋን በእጥፍ የሚያንሩ ነጋዴዎች በሕግ አግባብ ሊዳኙ እንደሚገባ አያጠያይቅም። ይህ እንዲሆን ግን የኅብረተሰቡ ተሳትፎና አጋርነት ሊኖር ግድ ነው። በገበያ ያልጠፋን ምርት አስቀድሞ አከማችቶ ጊዜን ጠብቆ በማውጣት ኑሮን የሚያከብዱ ስግበግቦች ጥቂት አይደሉም ።

ምንግዜም እንዲህ አይነቶቹ ድርጊቶች ከኅብረተሰቡ ዓይን አይሰወሩምና ለተገቢው አካል ተጨባጭ መረጃዎችን በማድረስ ኃላፊነትን መወጣት ይገባል። ይህ አይነቱ ጥቆማ የሚደርሳቸው አካላትም ራሳቸውን ከሙስናና ካልተገባ ጥቅም አርቀው ለኅብረተሰቡ መወገን ይኖርባቸዋል። የተረባረቡ እጆች ለኑሩ ውድነቱም ሆነ ለሌሎች ችግሮች መፍትሔ ይሆናሉና። ለክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች በሙሉ መልካም የገና በዓል ይሁን።

# ለገና በዓል - የእንስሳት ገበያው ድባብ

**ማርቆስ በላይ**



በኢትዮጵያ በድምቀት ከሚከበሩ ዓመታዊ ክብረ በዓላት መካከል በክርስትና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት የገና በዓል አንዱ ነው።

የገና በዓል ሲታሰብ የተለያዩ የበዓል ማድመቂያ ዝግጅቶች ይከናወናሉ። የተለያዩ የበዓል ምግቦችን በማዘጋጀት ከቤተሰብ እስከ ወዳጅ ዘመድ ተሰባስቦ በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ማክበር የተለመደ ነው። በዶሮና በበግ በፍየል እና በበሬ ሥጋ፣ ቤት ያፈራው ተሠርቶ ዕለቱን በደስታ እንዲያልፍ ሽር ጉዱ ብዙ ነው።

በበዓሉ ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ክዋኔዎች እንዳሉ ሆነው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችም ይበረቱበታል።

ገናን አስመልክቶ ያለውን ሁኔታ ለመቃኘት በዚሁ በመዲናችን በኮተቤ ብረታ ብረትና በአዲሱ ገበያ የሚገኙ የበሬና የበግ ገበያዎች ላይ ተዘዋውረን የበዓል ገበያ ውሎዎችን ቃኝተናል።

በኮተቤ ብረታ ብረት የእንስሳት ነጋዴ የሆኑት አቶ ኃይሌ አማረ ፍየል ነጋዴ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት በዘንድሮው ዓመት በትራንስፖርት ችግርና በመኖ መወደድ ሳቢያ ለበዓል ገበያ የቀረቡት ፍየሎች ዋጋቸው ጨምሯል።

በስፍራው ለገበያ የቀረቡ ፍየሎች እንደየክብደት መጠናቸው ለሸማች እየቀረቡ ናቸው የሚሉት ነጋዴው፤ ፍየሎቹ ከዘጠኝ ሺህ ጀምሮ እስከ 25 ሺህ ብር እንደገዢው ምርጫ እየቀረቡ ነው ባይ ናቸው።

ካለፉት በዓላት ጋር ሲነጻጸር ጭማሪ ማሳየቱን የሚናገሩት አቶ ኃይሌ፤ በትራንስፖርት ችግር ምክንያት የአቅርቦት ሁኔታውም እምብዛም ነው ሲሉ ነው የተናገሩት።

በዚሁ በኮተቤ ብረታ ብረት የፍየል ነጋዴ የሆኑት አቶ ካሣዬ ነጋ በአቶ ኃይሌ ኃሳብ አይስማሙም። በገበያው በርካታ ፍየሎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረባቸውን የሚገልጹት የሚናገሩት አቶ ካሳዬ፤ የፍየልና የበግ ገበያ አቅርቦቱ ከአምናው ዘንድሮ የተሻለ ነው ባይ ናቸው።

የዘንድሮ የበዓል ገበያ ጥራት ላይ ያተኮረና ዋጋውም ከወቅቱ አንጻር ተመጣጣኝ እንደሆነ ነው የሚናገሩት።

የኮተቤ የእንስሳት ገበያ በርካታ የቁም እንስሳት ለገበያ የሚቀርቡበት በመሆኑ የዘንድሮው የገና በዓል ካለው ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር እንደ ሌላው ጊዜ ባይሆንም የተወሠነ ድምቀት ታይቶበታል ሲሉም ያስረዳሉ።

ለገና በዓል ፍየል ለቤተሰቦቹ ለመግዛት ወደገበያው የመጣው ወጣት ዳመነ ኤርሚያስ የፍየል ዋጋ የሚቀመስ አልሆነም ይላል። ሆኖም በዓል በመሆኑ ቤተሰቡን ለማስደሰት እንደአቅሙ ገዝቶ ለመሄድ መወሰኑን ያስረዳል።

በገበያው ለበዓል እርድ የሚውሉ በርካታ እንስሳት ቢቀርቡም መጠነኛ የዋጋ ጭማሪ ማሳየቱን ተከትሎ የተቀዛቀዘ ገበያ መሆኑን ኢፕድ መታዘብ ችሏል።

በአዲሱ ገበያ በሬ ተራ ያገኘናቸው አቶ አበራ አዱኛ ደግሞ፤ በዘንድሮው የገና የበዓል ገበያ አነስ ያለ በሬ እስከ 35 ሺህ ብር ዋጋ የሚያወጣ መሆኑን ይገራሉ። ትላልቅና የደለቡ በሬዎች ደግሞ ከ85 ሺህ ጀምሮ እየተሸጡ መሆኑን ነው የሚናገሩት።

ገበያው ከቀን ወደቀን እየተሻሻለ እንደሚመጣ ተስፋ አድርገው በዋዜማው ደግሞ የተሻለ ግብይት እንደሚኖር ይጠበቃል ሲሉ ያስረዳሉ።

ለሸመታ የመጡት አቶ ቶልቻ አበበ ከጓደኞቻቸው ጋር ለበዓሉ የቅርጫ በሬ ለመግዛት ገበያ ውስጥ አግኝተናቸዋል። አቶ ቶልቻ፤ የበሬ ዋጋ ካለፉት የበዓላት ጊዜያት ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ የዋጋ ጭማሪ መኖሩን አስተውያለሁ ይላሉ።

ሆኖም ተዟዙረው ተመልክተው ለቅርጫ የሚሆን መካከለኛ በሬ በ65 ሺህ ብር መግዛታቸውን ይናገራሉ።

ሌላው በዚሁ ገበያ ያገኘናቸው አቶ ተሾመ ተካ በበኩላቸው፤ ከባለፈው ዓመት በዓል ጋር ሲነጻጸር የበግ ገበያው ዋጋ ጭማሪ ማሳየቱና በግ ከአምስት ሺህ ብር ጀምሮ እስከ 18 ሺህ ብር እየተሸጠ እንደሚገኝ ይናገራሉ።

እኛም በተዘዋወርንባቸው የኮተቤ ብረታ ብረት በሬና በግ ተራ እንዲሁም በአዲሱ ገበያ በሬ ተራ ገበያዎች ላይ ባደረግነው ምልከታ የዘንድሮው የበዓል ገበያ በርካታ ለእርድ የሚሆኑ በሬዎች የቀረቡበት ሲሆን፤ ከወትሮው ባነሰ መልኩ የበግና የፍየል አቅርቦት ተስተውሏል። ይሁንና በቡድንም ሆነ በግል መጥተው በሬ አሊያም በግና ፍየል የሚገዙ ሸማቾችን ነጋዴዎች በተለመደ ቅልጥፍናቸው እያስተናገዱ ይገኛል።

# በዲፕሎማሲ ሳምንት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

24 ቀን 2016 ዓ.ም የሚከበረውን የዲፕሎማሲ ሳምንት አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ሰጥቷል፡፡

መግለጫውን የሰጡት የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ከጥር 2 እስከ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የዲፕሎማሲ ሳምንት ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ይካሄዳል፡፡ የዲፕሎማሲ ሳምንቱ በተለያዩ ፕሮግራሞች የሚከናወን ሲሆን ‹‹ከአፍሪካ መዲና እስከ ዓለም መድረክ›› በሚል መሪ ቃል የሚከበር ይሆናል፡፡

ለሺህ ዘመናት የቆየ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ

አላት ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ከቅርብና ሩቅ ካሉ ሀገሮች ጋር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት አላት ብለዋል።

በዲፕሎማሲ ሳምንቱ የጥንቱ ብቻ ሳይሆን አሁንም በዓለም መድረክ ተፅዕኖ መፍጠር የምትችል ሀገር መሆኗን ለማሳየት የሚያስችል የአሁኑ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ይዳሰሳል። ቀጣይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ስኬታማ እንዲሆን የዲፕሎማሲ አቅሟን የበለጠ ማጠናከር ተገቢ ነው ብለዋል።

ለሦስት ሳምንት በሚቆየው የዲፕሎማሲ ሳምንት በርካታ ሁነቶች አሉ ያሉት አምባሳደር መለስ፤ የመጀመሪያው ዓውደ ርዕይ ሲሆን ከጥር ሁለት ጀምሮ በሳይንስ ሙዚየም የሚካሄድ ይሆናል። ይሄ በፎቶና በቪዲዮ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰነዱ የሀገር ሀብቶች ለዕይታ የሚቀርቡበት ይሆናል ሲሉም ገልጸዋል።

አምባሳደር መለስ እንዳሉት፤ የጥንቱን የዲፕሎማሲ ተሳትፎ፣ የአሁኑንና የመጪ ዘመን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ለማሳየት ይሞከራል። ዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት ሥራው የአጭር ጊዜ ታሪክ ሳይሆን ኢትዮጵያን ያህል እድሜ ያለው ነው።

ጥንታዊው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ለአሁኑ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ መሠረት ነው ያሉት ቃለ አቀባዩ፤ ኢትዮጵያ እምቅ የሆነ የዲፕሎማሲ አቅምና ሀብት እንዳላት በመገንዘብ አሁን ያለውን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ የሚዘከር መሆን አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

ከአፍሪካ መዲና እስከ ዓለም መድረክ የሚለው መሪ ቃል ትልቅ ትርጉም አለው ያሉት አምባሳደር መለስ፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቀመጫ ነበረች። አሁን የአፍሪካ ኅብረትም መቀመጫ ናት። በሁለቱ ተቋማት ምሥረታ ላይ ጉልህ ሚና አላት። ይህን አበርክቶዋን በሚገባ ለዓለም የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰቡ ማሳየት አስፈላጊ ነው። እስከ ዓለም መድረክ የተባለበት ምክንያት ኢትዮጵያ የበርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሥራችና ንቁ ተዋናይ መሆኗን ለማመላከት ነው ብለዋል።

ሊግ ኦፍ ኔሽን ከመመሥረቱ ቀደም ብሎ በነበሩ በርካታ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ኢትዮጵያ የመሥራችነት ሚና ነበራት ያሉት አምባሳደሩ፤ የዓለም ፖስታ ኅብረት፣ የዓለም አቀፍ ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኅብረት፣ የዓለም አቀፍ አቪዬሽንና በሌሎች ድርጅቶች ላይ ንቁ ተሳትፎ ነበራት ብለዋል። እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሲመሠረት ቻርተሩን በፊርማቸው ካፀደቁ ጥቂት ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ተጠቃሽ መሆኗንም አብራርተዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ ማብራሪያ፤ በገለልተኛ ሀገራት ንቅናቄ ውስጥ ኢትዮጵያ መሥራች ነበረች። በሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማትም ትልቅ አስተዋፅዖ አላት። የዲፕሎማሲ ሳምንቱም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ውስጥ ያላትን ንቁ ተሳትፎና ሚና ለማሳየት የሚያስችል ነው።

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ ዓውደርዕዩ የጥንቱን፣ የአሁኑንና የመጪውን ጊዜ የሚያመላክት እንዲሆን ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የፓናል ውይይት መድረክ የዲፕሎማሲ ሳምንቱ አካል ሲሆን የጥንቱ፣ የአሁኑና የመጪው ጊዜ ዲፕሎማሲ ይዳሰስበታል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 116 ዓመቱን ባለፈው ጥቅምት ወር አስቧል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ከተቋቋሙ አስር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ውስጥ አንዱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደነበረና የውጭ ጉዳይና የንግድ ሚኒስቴር ተብሎ መቋቋሙን ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያን 116 ዓመት የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ የሚዳስስ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ታሪክ ከ1900 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም የሚል መጽሐፍ በይፋ ለአንባቢያን ይቀርባል። በቀጣይ መደበኛ ሊሆን የሚገባው የዲፕሎማቲክ ጆርናል ስለመዘጋጀቱም ቃል አቀባዩ ገልጸዋል።

# በዓላትን ተከትሎ የአቅርቦት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

ለገናና ለጥምቀት በዓል የሚያስፈልጉ ምርቶች በበቂ ሁኔታ ለገበያ እየቀረቡ በመሆኑ ማኅበረሰቡ ተረጋግቶ ግብይት ማድረግ አለበት ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዓላቱ የሚከበሩት በመኸር ወቅት በመሆኑ በቂ የሆነ ምርት እንዳለም አብራርተዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ እንቁላል ከስምንት ሚሊዮን በላይ የቀረበ መሆኑን የተናገሩት አቶ ፍስሐ፤ በክልሎች እንደየፍላጎታቸው መጠን በስምንት ብር ሂሳብ እንቁላል ተሠራጭቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም አንድ ሚሊዮን ዶሮ በማዘጋጀት ለአዲስ አበባ 93 ሺህ፤ ለኦሮሚያ 179 ሺህ 868 እና ለደቡብ ኢትዮጵያ 119 ሺህ 36 ዶሮዎችን ከ450 እስከ 750 ብር ዋጋ የማሰራጨት ሥራ ተከናውኗል ሲሉ አክለዋል፡፡

ከ500 ሺህ በላይ ሰንጋ በሬዎች እና 600 ሺህ ፍየልና በግ የማቅረብ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ ፍስሐ፤ የአንድ ሰንጋ በሬ ዋጋ ከ65 ሺህ ብር እንደሚጀምርም ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም ዘጠኝ ነጥብ 8 ሚሊዮን ሊትር ዘይት የሚቀርብ መሆኑን ጠቅሰው፤ ስምንት ነጥብ 6 ሚሊዮን ሊትሩ ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ሁለት ሺህ 710 ሸማች ሥጋ ቤቶች ለግብይት እንደተዘጋጁ ጠቁመው አንድ ኪሎ ስጋ 450 ብር የሚሸጥ ይሆናል ብለዋል፡፡

ኅብረተሰቡ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋና በወጣላቸው ተመን እንዲገበይ ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ ነው ሲሉ አመላክተዋል።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሀገር ውስጥ ንግድና ሸማቾች መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ መስከረም ባሕሩ በበኩላቸው፤ በበዓላት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

የምርት የዋጋ ንረትን ለመከላከል እየተሠራ ነው ያሉት ሥራ አስፈፃሚዋ፤ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎችም አቅርቦትን ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

ሦስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሊትር የዘይት ምርትም ወደ አማራ ክልል ተደራሽ ሆኗል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በበዓላት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰት ከማድረግ በተጨማሪ ምርቶች ከወጣላቸው የዋጋ ተመን ውጪ እንዳይሸጡ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉም አመላክተዋል፡፡

# ብዝኃነትን መቀበል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አቀፍ የአብሮነት ቀን የማጠቃለያ መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

በመድረኩ የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በእኩልነትና በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ብዝኃነትን መቀበል የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የሕልውና ጉዳይ ነው።

ኅብረ ብሔራዊነትና ብዝኃ ባሕል የኢትዮጵያውያን መገለጫ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህም በአብሮ መብላትና መጠጣት፣ እርስ በርስ በመጠያየቅ፣ በመረዳዳት፣ የተጣላን በማስታረቅ ወይም በሽምግልና፣ በሃይማኖተኝነትና በጀግንነት ይገለጻል ብለዋል።

በኢትዮጵያ አብሮነትን መሠረት ያደረገ ሥርዓት ለመገንባት ብዝኃነትን መቀበል፣ ዜጎች በነፃነት፣ በእኩልነትና በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት እንደሚያስፈልግም አስረድተዋል።

ኢትዮጵያውያን ሀገረ መንግሥት ለመገንባት የሚያደርጉት ትግል ብዙ ፈተናዎች ያሉበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሂደቱ ጽንፈኝነትን በመመከት፤ የማንነት፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና የባሕል ብዝኃነትን በማክበር ልማትና ዴሞክራሲን ለማስፋት በቁርጠኝነት መሥራት ይገባል ብለዋል።

የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ወርቅነሽ ብሩ በበኩላቸው፤ የአብሮነት ቀን መከበሩ በኅብረተሰቡ መካከል የመከባበርና መቻቻል፤ መደጋገፍ፤ የሠላም እና አብሮነት ግንባታ አስተሳሰብ እንዲጎለብት ያደርጋል ብለዋል።

ይህም ኅብረተሰቡ ስለአብሮነት ያለውን አመለካከት በሚያጠናክር ሁኔታ ቀጣይ ሥራዎች ላይ በቀጥታ በመሳተፍ ሃሳቡን እንዲያዳብር በማድረግ አብሮነቱን እና ሀገራዊ አንድነቱን እንደሚያጠናክር ገልጸዋል።

በመድረኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ የፓናል ውይይት የተካሄደ ሲሆን የፓናል ውይይቱን ሲመሩ የነበሩት የሠላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ከይረዲን ተዘራ፤ ኢትዮጵያውያን እጅግ የተሳሰሩና የተጋመዱ፣ በመንፈስ የተገናኙ እና በአኗኗር ዘይቤ ትስስር ያላቸው ናቸው ሲሉ ገልጸዋል።

ይህ ኢትዮጵያውያንን ከሌላው ዓለም ሕዝቦች በልዩ ሁኔታ እንዲታዩ ያደርጋቸዋል ብለውም፤ በዚህም አንድነታቸውና አብሮነታቸው ይገለጻል ብለዋል። አብሮነት ወሳኝና አስፈላጊ ጉዳይ ነው ያሉት ደግሞ የውይይት መነሻ ጽሑፍ ያቀረቡት ዶክተር ገመቹስ ደስታ ናቸው።

አብሮነት ለማኅበራዊ ባሕላዊ እሴቶችና ለሰላም ግንባታ ወሳኝ ነው ያሉት ዶክተር ገመቹስ፤ አብሮነት መከባበርን፣ መደማመጥን፣ ብሔራዊ መግባባትን መሠረት አድርጎ የሚገነባ ስለመሆኑ አንስተዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ26ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ14ኛ ጊዜ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የአብሮነት ቀን ምክንያት በማድረግ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ከታኅሣሥ 20 እስከ 25 ቀን 2016 ዓ.ም "ብዝኃነትን መኖር" በሚል መሪ ሀሳብ በባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር በተለያዩ ሁነቶች ሲከበር መቆየቱ ይታወሳል።

# "ብልጽግና ለሀገርና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርሕን መሠረት ባደረገ ሠላማዊ በሆነ ሁኔታ ለማሳካት ቁርጠኝነት ያሳየችበት ታሪካዊ ሁነት መሆኑን ገልጸዋል። በቀጣይ ፓርቲውን በማጠናከር የሕዝቡን አቅም በመጠቀም ወዳጆችን በመብዛት ከጎን የማሰለፍ ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

የፓርቲ ጥንካሬ የሚለካው በሀሳብ ጥራት፣ በአመራርና አባላት ጥራት፣ በአሠራር ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን፣ ቅቡልነት ማኅበራዊ መሠረትን በማጠናከርና በአደረጃጀት ጥንካሬ መሆኑን አቶ አደም ገልጸዋል። ከዚህ አንጻር ፓርቲው በየጊዜው የሚገጥሙትን ፈተናዎች በመቋቋም ዓላማውን እያሳካ በከፍታ ይጓዛል ብለዋል።

ለፓርቲው የፖለቲካ ጤነኝነት ለአመራሩንና አባላቱ የወጣውን የዲሲፕሊን መመሪያ በመተግበር ነባራዊ ሁኔታዎችን በመከተል ለሕዝብና ለሀገር የሚበጁ ሀሳቦችን በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ እያደረገ እንደሚቀጥል ጠቅሰዋል።

የፌዴራል ተቋማት የብልጽግና ፓርቲ አደረጃጀት አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር) ፓርቲው ባለፉት አምስት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ስኬቶችን በተጨባጭ ማስመዝገቡ በመድረኩ ተናግረዋል። ፓርቲው በተለያዩ ሥራዎች ካስመዘገበው ስኬት ባሻገር የአባላት መዋጮን በ2012 ዓ.ም ከነበረበት አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በ2015 ዓ.ም ወደ ስምንት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ማሳደግ መቻሉን አስታውቀዋል።

አመራሩና አባሉ የፓርቲን ሥራ በትኩረትና ቁርጠኝነት መፈጸም መቻላቸው ፓርቲውን ስኬታማ ማድረግ እንደቻለም ገልጸዋል።

በመርሐ ግብሩ በፓርቲው በ2015 ዓ.ም የሥራ አፈጻጸም የላቀ ውጤት ላመጡና ከእዳ ወደ ምንዳ በሚል መሪ ቃል ሲሰጥ የቆየው ሥልጠና በስኬት እንዲጠናቀቅ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ተቋማትና ግለሰቦች እውቅና ተሰጥቷል።

በመድረኩ ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ከሶማሊላንድ ጋር መፈራረሟን አስመልክቶ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮችና አባላት የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል።

ስምምነቱን ለፈረሙት ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ምስጋና ቀርቧል።

በመርሐ ግብሩ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮችና አባላት እንዲሁም የተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።

# አብሮነት - ለኢትዮጵያዊ ብዝሀነት

አንተነህ ቸሬ

ከሰው ልጅ ባህርያት መካከል አንዱ አብሮነት ነው። አብሮ መሥራት፣ አብሮ መንቀሳቀስ ... አብሮ መኖር የሰው ባህርያትና ድርጊቶች ናቸው። የማኅበራዊ ሳይንስ ጥናት ባለሙያዎችም ሰው በባህሪው ማኅበራዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻውን ከመኖር ይልቅ አብሮ መኖርን እንደሚመርጥ በጥናት አስደግፈው ይገልፃሉ። የሃይማኖት መምህራንም ፈጣሪ ሰውን ፈጥሮ ብቻውን ሊተወው ስላፈለገ አጋዥ/አጋር እንደፈጠረለት በመናገር አብሮነት በፈጣሪም የሚደገፍ እንደሆነ ያስተምራሉ።

አብሮነት መቻቻልና መተባባር የጠነከረበት እንዲሁም ዘላቂ ሰላም የሰፈነበት ማኅበረሰብ/ሀገር ለመገንባት በጎ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የማኅበረሰብ ጥናት ባለሙያዎች ደጋግመው ያስረዳሉ። በአብሮነት ውስጥ ሰው መሆንንና የማንነት መገለጫዎቻችን ማክበር፣ መቀበልና ማድነቅ አለ። አብሮነት የተለያዩ ማንነቶችን ያስተናግዳል፤ ያከብራል። አብሮነት የሰዎችን መስተጋብር ያቀናጃል፤ ያጠነክራል። አብሮነት በሰላም አብሮ የመኖር መሠረት ነው።

በርካታ ግለሰቦችና ተቋማት በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚስተዋሉት ግጭቶች እንዲሁም የጥላቻ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ለአብሮነት አስተሳሰብ ተገቢውን ስፍራ ያለመስጠት ውጤቶች አድርገው ይመለከቷቸዋል። በርግጥም የመቻቻልና የአብሮነት እሳቤና ተግባር ተገቢውን ትኩረት ቢያገኝ ኖሮ፣ ከባድና አሳዛኝ ዋጋዎችን ያስከፈሉት ብዙዎቹ አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዳይከሰቱ ማድረግ ይቻል ነበር።

ስለሆነም ስለአብሮነትና መቻቻል በመነጋገርና ግንዛቤ በመፍጠር ግጭቶችን ለማስወገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር "የመቻቻል ቀን" እንዲኖር በቀረበ የመነሻ ሃሳብ መሠረት፣ እ.ኤ.አ ከ1995 ጀምሮ "ዓለም አቀፍ የመቻቻል ቀን" (International Day for Tolerance) በየዓመቱ ኅዳር 6 ቀን (November 16) ይከበራል። "ዓለም አቀፍ የመቻቻል ቀን" የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ተቋም (ዩኔስኮ) እ.ኤ.አ በ1995 ባቀረበው የመነሻ ሃሳብና የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባዔ ባፀደቀው ውሳኔ (የውሳኔ ሃሳብ 15/95) መሠረት፣ የድርጅቱ አባላት በሆኑ ሀገራት የሚከበር ሲሆን፣ የቀኑ መከበር ዋና ዓላማም ስለመቻቻል ምንነትና ፋይዳ ግንዛቤ መፍጠር ነው። በ"መቻቻል ቀን" በርካታ ልዩነቶች ባሉበት ዓለም ውስጥ የመቻቻል እሳቤና ተግባር ስላለው ጥቅም በስፋት ይነገራል። የዘንድሮው "ዓለም አቀፍ የመቻቻል ቀን" "መቻቻል፣ የሰላምና የእርቅ መንገድ" በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ26ኛ ጊዜ ተከብሯል።

በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች መፍትሔ እንደሆነ የሚታመንበት አብሮነት፣ የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነና የእርስ በእርስ ማኅበራዊ መስተጋብራቸውን አጠንክሮ የኖረ ተግባር ነው። የተራበን ማብላት፣ የታረዘን ማልበስ፣ ያዘነን ማፅናናት... የተቸገረን መርዳት ኢትዮጵያውያን የሚታወቁበት ባህርያቸው እንዲሆን ያደረገው የአብሮነት ባህል ነው። ደስታና ሐዘናቸው በአብሮነት ነው። ኢትዮጵያ ያለ ኢትዮጵያውያን አብሮነት ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ መቆየት አትችልም ነበር። በአጠቃላይ፣ አብሮነት ባይኖር ኖሮ አሁናዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የተለየ ይሆን ነበር።

ቴክኖሎጂው፣ የሕይወት ሩጫው፣ የእርስ በእርስ ፉክክሩ... የበዛበት ዘመናዊው ዓለም ግን ከአብሮነት ጋር የሚስማማ ሆኖ አይታይም። "አብሮነት ተዳከመ፣ መተባበርና መደጋገፍ ጠፋ ..." የሚሉ ድምጾች ደጋግመው ይደመጣሉ። በተለይም የኢትዮጵያውያን መገለጫ ተደርገው ከሚቆጠሩት ባህርያት መካከል አንዱ የሆነው አብሮነት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረና እየደከመ መሄዱ ያሳሰባቸው ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ይስተዋላል።

የጳጉሜን ወር ቀናት በተለያዩ ስያሜዎች ሲከበሩ ለቀናቱ ስያሜነት ከሚሰጡ ሃሳቦች መካከል አንዱ አብሮነት/መቻቻል/ ነው። ለአብነት ያህል ያለፈው ዓመት የጳጉሜን ወር ስድስተኛ ቀን "የአብሮነት ቀን" ተብሎ ተሰይሞ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደተከናወኑበት ይታወሳል።




አብሮነት መገለጫዋ የሆነውና በየዓመቱ "ዓለም አቀፍ የመቻቻል ቀን"ን ስታከብር የቆየችው ኢትዮጵያ፣ የዘንድሮውን "ዓለም አቀፍ የመቻቻል ቀን" ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ ቀኑን የ"አብሮነት ሳምንት" በሚል ስያሜ አክብራለች። የዘንድሮው "የአብሮነት ሳምንት"፣ "ብዝሀነትን መኖር" በሚል መሪ ቃል ከታኅሣሥ 20 እስከ 25 ቀን 2016 ዓ.ም ለ14ኛ ጊዜ የተከበረ ሲሆን፤ በኅብረተሰቡ መካከል የመከባበር፣ የመቻቻል፣ የአብሮነት እና የሰላም ግንባታ አስተሳሰብ እንዲጎለብት የሚያስችሉ ተግባራት እንዲከናወኑ እና ሀገራዊ አንድነትንና አብሮነትን በሚያጎላ መልኩ እንዲከበር ጥረት ተደርጓል። ይህን ጥረት ስኬታማ ለማድረግም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተመራ ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ለዝግጅቱ ስኬት የሚረዱ ተግባራትን አከናውኗል።

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የቋንቋ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ወርቅነሽ ብሩ "የአብሮነት ሳምንት" መከበር የኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያን/ መገለጫ የሆነውን የአብሮነት ባህል የበለጠ ለማጉላት ፋይዳ እንዳለው ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ አብሮነት ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ያዳበሩት እሴት በመሆኑ፣ የሳምንቱ ስያሜ ለዚህ አስተሳሰብና ድርጊት የበለጠ ተስማሚና ገላጭ ይሆናል። አብሮነት በብሔር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በሌሎች የማንነት መገለጫዎች የተለያዩ ወገኖችን የሚያቀራርብና የሚያስተሳስር እሴት ነው። ቀደምት አባቶቻችን ኢትዮጵያን ከትውልድ ትወልድ ለማስተላለፍ የተጠቀሙት ትልቁ እሴትና መሳሪያ አብሮነት ነው።

"ኢትዮጵያ በብዙ የማንነት መገለጫዎች (እምነት፣ ብሔር፣ ቋንቋ...) የብዝሀነት ባለቤት ናት። ኢትዮጵያውያን በአብሮነት መንፈስ በአንድነት ቆመው ሀገርን ለማስቀጠል የከፈሏቸው መስዋዕትነቶችም አፍሪካንና ዓለምን ያስደመሙ ናቸው። የኢትዮጵያውያን መገለጫዎችና ድርጊቶች በአብሮነት የሚከወኑ ናቸው። "የአብሮነት ሳምንት" እነዚህ መገለጫዎች ይበልጥ እንዲጎሉና እንዲደምቁ ያደርጋል» ይላሉ።

"የአብሮነት ሳምንት» ሲከበር የአሁኑ ትውልድ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ከነበራቸው የአብሮነት ባህል ምን መማር እንዳለበት፣ ትውልዱ ያጎደላቸው የአብሮነት እሴቶች ምን እንደሆኑ እና ጠንካራ የአብሮነት መንፈስ ለመፍጠር ምን ማድረግ እንደሚገባ እንዲሁም ቀደምት ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን የአብሮነት መንፈስ መጠበቅና ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር እንደሚያስፈልግ መገንዘብ እንዳለበትም ይናገራሉ።

እንደ ወይዘሮ ወርቅነሽ ማብራሪያ፤ ጉዳዩ የአንድ ግለሰብ ወይም ተቋም ብቻ ባለመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኝ ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ፣ ብሔራዊ ኮሚቴው በቴክኒክና ንዑሳን ኮሚቴዎች ተደራጅቶ ዝግጅቱን ለማድመቅ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ተግባራት ተከናውነዋል። ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት ተቋማት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሚያስተባብረው ብሔራዊ ኮሚቴ አባል ሆነው በቴክኒክና ንዑሳን ኮሚቴዎች ተግባራት ውስጥ በንቃት ተሳትፈዋል።

በ‹‹አብሮነት›› ሳምንት አብሮነትን በተግባር ለማሳየት የታመሙ ሰዎችን የመጠየቅ፣ የተቸገሩ ወገኖችን የመርዳት፣ ደም የመለገስ፣ ስለአብሮነት ምንነትና ፋይዳ በመገናኛ ብዙኃን ገለፃዎችን የማቅረብ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ስለአብሮነት ያለውን እሳቤ እንዲናገር እድል የሚሰጡ የውይይት መድረኮችን የመፍጠር፣ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በጋራ የመሥራት እና በአብሮነት ላይ ያተኮሩ መልዕክቶችን የመለዋወጥ ተግባራት ተከናውነዋል። ከዚህ በተጨማሪም የመንግሥት ሹማምንት፣ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች፣ ምሁራን፣ አምባሳደሮችና የኅብረተሰብ ተወካዮች የሚሳተፉበት የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በ‹‹አብሮነት›› ሳምንት አብሮነትን በተግባር ለማሳየት የታመሙ ሰዎችን የመጠየቅ፣ የተቸገሩ ወገኖችን የመርዳት፣ ደም የመለገስ፣ ስለአብሮነት ምንነትና ፋይዳ በመገናኛ ብዙኃን ገለፃዎችን የማቅረብ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ስለአብሮነት ያለውን እሳቤ እንዲናገር እድል የሚሰጡ የውይይት መድረኮችን የመፍጠር፣ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን በጋራ የመሥራት እና በአብሮነት ላይ ያተኮሩ መልዕክቶችን የመለዋወጥ ተግባራት ተከናውነዋል

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኮራ ጡሽኔ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የ‹‹አብሮነት ሳምንት›› መከበር አብሮነት በአሁኑ ወቅት አደጋ ውስጥ እንደገባና ለዚህም መፍትሔ የሚሆን አቅጣጫ ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንደሚያግዝ ይገልፃሉ።

"የሰው ልጅ ስልጣኔ መሠረት አብሮነት ነው። በጥንት ጊዜ የሰው ልጅ ተበታትኖ በሚኖርበት ዘመን ሕልውናው ጭምር ለአደጋ የተጋለጠ ነበር። በአብሮነት መኖሩ ጥንካሬ ሆኖታል። በአሁኑ ጊዜ አብሮነት በቴክኖሎጂ ነክ ጫናዎችና በሌሎች ምክንያቶች እየተሸረሸረ ነው። አብሮነት ፈተና ውስጥ በገባበት ጊዜ ላይ ስለምንገኝ ስለአብሮነት ደጋግሞ መናገር ይገባል" ይላሉ።

ዶክተር ኮራ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮነትን በእጅጉ የሚፈልግና በአብሮነት የኖረ ኅብረተሰብ እንደሆነ ጠቁመው፣ ሕዝቡ የአብሮነትን እሴት በሚገባ የሚያውቀውና የኖረበት ባህሉ በመሆኑ፣ ይህን እሴት ጠብቆ በማቆየት ጠንካራ ሀገር መገንባት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተለያዩ ባህርያትና የማንነት መገለጫዎች ባለቤት የሆኑ ተማሪዎች የሚገናኙባቸው ስፍራዎች ስለሆኑ፣ ጠንካራ የአብሮነት እሴት ሊታይባቸው የሚገቡ ቦታዎች መሆን አለባቸው። በተቋማቱ ውስጥ የሚታዩ የአብሮነት እሳቤዎችና ተግባራት ለሀገርም ጠቃሚ ይሆናሉ። "አብሮነት ከሌለ ሰላም፣ ልማት፣ ፍትህና እኩልነት አይታሰብም" የሚሉት ዶክተር ኮራ፣ የልዩነትን ተፈጥሯዊነት ጠብቆ በአብሮነት ላይ ማተኮር ይገባል በማለት ይናገራሉ።

የአብሮነት እሳቤና ተግባር በሃይማኖት ተቋማት በእጅጉ የሚደገፍ ነው የሚሉት የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ተወካይ አቶ ተስፋዬ ውብሸት፤ አብሮነት በሁሉም የሃይማኖት አስተምህሮዎች ውስጥ የተካተተ የበጎ እሳቤ መገለጫ እንደሆነ ያስረዳሉ። "አብሮነት ጥንትም የነበረና ወደፊትም የሚኖር ነው። በአብሮነት ውስጥ ሰላም፣ አንድነት፣ ፍቅርና መተባበር አለ። የአብሮነት እሴቶችና ተግባራት በሁሉም ቤተ-እምነቶች አስተምሮዎች ውስጥ አሉ። አብሮነት የሁሉም ሃይማኖቶች ዕለታዊ ትምህርት አካል ነው" በማለት ስለአብሮነት ፋይዳና አብሮነት በሃይማኖቶችም የሚደገፍ ተግባር እንደሆነ ያስረዳሉ።

አቶ ተስፋዬ እንደሚናገሩት፣ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ባለፉት 13 ዓመታት አብሮነትን ለማጠናከር የሚያግዙ ተግባራትን አከናውኗል። ጉባዔው በመላው ኢትዮጵያ ባሉት መዋቅሮች፣ በተለይም አብሮነት ለሰላም መስፈን ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው፣ በከፍተኛ ትኩረት ተንቀሳቅሷል። ስለአብሮነት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ የማስተማሪያ ሰነዶች አዘጋጅቶ ስለእሳቤው ትምህርት ይሰጣል። እስካሁን የተከበሩ የአብሮነት ቀናት ሰላምን በማስፈን እና ግጭቶችን በመፍታት ረገድ ቀላል የማይባሉ በጎ አስተዋፅኦዎችን አበርክተዋል። አብሮነትን የበለጠ ለማዳበር ተስማምቶ መሥራትን እንደሚጠይቅም አቶ ተስፋዬ ገልጸዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ደግ ልቦች

ክብረአብ በሳቸው

በጎነት የሚታይ ፍሬ ነው። የሕይወትን ጎተራ የሚሞላ ለግለሰብና ለሀገር የሚተርፍ ተግባር፤ በጎነት ከማሰብ በዘለለ፤ አብዝቶ ከመልካም ሥራዎች ጎን መሰለፍን፣ ሌሎችን ማገዝ ላይ ማተኮርን ከሰው ምላሽ ሳይጠብቁ ከራስ በላይ ለሌሎች ማድረግን የሚጠይቅ የንፁህ ልብ ክዋኔ ነው።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ደግሞ ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነትና መልካም ፈቃድ በኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በማሳተፍ ነፃ አገልግሎት የሚያበረክቱበት ተግባር ነው፡፡ ይህ አገልግሎት የሰው ልጅ ምንም ዓይነት ክፍያ የማያገኝበት ያስደስተኛል፣ የህሊና እርካታ ያስገኝልኛል፣ ይበጀኛል ብሎ ያለምንም ቀስቃሽና ጎትጓች በእራሱ ተነሳሽነት የሚፈፅመው ተግባር ነው፡፡

ይህ ተግባር ማንኛውንም ዜጋ የሚያሳትፍ ቢሆንም በዋናነት ግን ወጣቶችን በስፋት የሚመለከት ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ማኅበራዊ ትስስርን፣ አንድነትንና ፍቅርን የበለጠ እንዲጠናከር የሚያደርግ ስለመሆኑም ይነገራል፡፡ ከወጣት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ወጣት ሄኖክ ፍቃዱ አንዱ ነው፡፡

ሄኖክ ተዋልዶ ያደገው በመዲናችን አዲስ አበባ ኮልፌ አካባቢ ነው። ወጣቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ በጎ አድራጎት ሥራ የገባበትን አጋጣሚ ሲያስታውስ፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ኪሎ ካምፓስ ተማሪ በነበረበት ወቅት አዲስ ሕይወት የበጎ አድራጎት የሚባል ክበብ ውስጥ አብሮ በሚሰራበት ወቅት በአካባቢው ለአቅመ ደካሞች እና ለሕፃናት ድጋፍ ያደርግ ነበር፡፡ ለሕፃናት የመማሪያ ቁሳቁስ እንዲሟላላቸው ሲያደርግ ባየው የሕፃናቱ ደስታና ሳቅ በተሰማው ሀሴት መነሻ በጎነትን የሕይወቱ አንድ አካል አድርጎ ለመሥራት እንደወሰነ ይናገራል።

በመቀጠል ከባይሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ማህበር መስራቾች መካከል አንዱ የሆነው ሄኖክ ስለማህበሩ አመሠራረት ሲናገር፤ በኢኮኖሚ አቅማቸው እጅግ ደካማ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተቻለው አቅም ድጋፍ ለማድረግ በማሰብ እንደተመሠረተ ይናገራል። በመኖሪያ ሰፈሩ አካባቢ ካፍቴሪያ ውስጥ ተቀምጦ ጊዜ ከማባከን ለማኅበረሰብ ለሀገር የሚጠቅም ቁም ነገር ያለውን ሥራ ለምን አንሰራም? በማለት ከሰፈር ጓደኛሞች ጋር በመነጋገር አስር ከሚሆኑ አብሮ አደጎቹ ጋር አንድ ላይ በመሆን የተመሠረተ ስለመሆኑ ይናገራል።

ወጣት ሄኖክ እንደሚገልፀው፤ 20 ለሚሆኑ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ዩኒፎርም በማልበስ፣ ደብተርና እስኪርብቶ በመስጠት የተጀመረው ባይሽ ኮልፌ በኋላም ልጆች ወልደው ልጆቻቸው የሞቱባቸውን ወይም መሃን የሆኑ እናትና አባቶችን በማገዝ ቀጥሎ ዛሬ ላይ በብዙ መልኩ ለብዙዎች የሚተርፍ የበጎነት ቤት ሆኗል ይላል።

በአሁኑ ወቅት በባይሽ ኮልፌ ወርሃዊ አስቤዛ የምንዛላቸው በቋሚነት የሚረዱ ከሰማንያ በላይ የሚሆኑ ቤተሰቦች እንዳሉ የሚናገረው ሄኖክ፤ በሌላ መልኩ ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በክርስቲያንም ሆነ በሙስሊም በዓላት ላይ አብሮ በመሆን እንደሚያሳልፉ፣ በተጨማሪም የጠፉ ሰዎችን በማገናኘት፣ እነዚህ በቋሚነት የሚረዱትን ህመም በሚያጋጥማቸው ጊዜ የሕክምና ርዳታ እንዲያገኙ በማድረግ፣ መኖሪያ ቤታቸው በተለያየ ምክንያት የፈረሰባቸውን ሰዎች ቤታቸውን በማደስ፣ ጎዳና ላይ ያሉ ዜጎችን ደግሞ ከተለያዩ ማዕከላት ጋር በመነጋገር ወደ ማዕከል የሚያስገቡበትን ሁኔታ መመቻቸት፣ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ደግሞ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ያሉ ደጋግ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበር በውጭና በሀገር ውስጥ የሕክምና ዕርዳታ እንዲያገኙ በማድረግ እየሠራ እንደሆነ ይናገራል።

ጎዳናን ቤታቸው ያደረጉ በባይሽ ኮልፌ አማካኝነት ከጎዳና የራሳቸውን ቤት የሰሩና ሥራ ፈጥረው እርሳቸውን ከመቻል ባለፈ ሠራተኛ ቀጥረው ለሌሎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ፣ ለራሳቸው ጥሩ ኑሮ ከመምራት በዘለለ ለሌሎች መትረፍ የቻሉ እንዳሉ የሚናገረው ሄኖክ፤ በዚህም ትልቅ ደስታና እርካታ እንደሚሰማው ይገልጻል።

ወጣት ሄኖክ ከአዲስ ዘመን ጋር በነበረው ቆይታ ወጣት ሆኖ በበጎ አድራጎት ላይ መሳተፍ ምን ዓይነት ስሜት እንዳለው ሲናገር፤ በጎነት በቃላት የማይገለጽ ትልቅ ደስታና ዋጋ ያለው ነገር እንደሆነ ይገልፃል። የተከፉ ፊቶች በደስታ ሲሞሉ ማየት፣ ጠያቂና አጋዥ ለሌላቸው ሰዎች ጊዜ በመስጠትና አብሮ በማሳለፍ የሚገኘው ውስጣዊ ደስታ ትልቅ እንደሆነ ይናገራል።



በዚህ የበጎ አድራጎት ሥራ ውስጥ ብዙ ደስ የሚያሰኙ በዛው ልክ የሚያስከፉ አጋጣሚዎች ይኖራሉ የሚለው ወጣት ሄኖክ፤ ከፍተኛ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው በገንዘብ እጥረት ምክንያት ግን ሕክምና ማግኘት ተስኗቸው ሞታቸውን የሚጠባበቁ ሰዎች ለበጎነት በተዘረጉ እጆች እርብርብ ታግዘው ለሕክምናቸው የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ተሟልቶ ታክመውና ድነው ደስተኛ ሲሆኑ ማየት ያለው ስሜት በቃላት የማይገለጽ እንዳልሆነ ይናገራል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከፍተኛ እርብርብ ተደርጎ በብዙ ዋጋ መክፈል ለሕክምና የሚያስፈልጋቸው በብዙ ሚሊየን የሚቆጠር የገንዘብ ወጪ አሁንም ለደግነት በተዘረጉ እጆች ድጋፍ ተሟልቶ ሕይወታቸው የሚያልፍ ሰዎች ይኖራሉ የሚለው ሄኖክ፤ እነዚህ አጋጣሚዎች ደግሞ ልብ የሚያሳዝኑ እንደሆኑ ይናገራል።

በጎነት የሚጀምረው ከሰፈርና ከጎረቤት ነው የሚለው ወጣት ሄኖክ፤ በጎ አድራጎትን በተመለከተ አሁን ላይ ያለው የሰው አመለካከት እየተሻሻለ የመጣና ይበል የሚያሰኝ ነው፤ ለዚህም አሁን ባይሽ ኮልፌ ያለበት ሁኔታ ዓይነተኛ ምስክር መሆን የሚችል ነው ይላል። ብዙ ቁጥር ያለው ድጋፍ የሚደረግለት ሰው ቅን ግለሰቦች በሚያወጡት ገንዘብ መሆኑን በማስታወስ፤ ለበጎ ሥራ እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች እንደሚተጉ ይናገራል።

አሁንም ግን ጎዳና ለወደቁ ዜጎች ማኅበረሰቡ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ማደግ ያለበት ነው የሚለው ወጣት ሄኖክ፤ በኢትዮጵያ ካለውና ርዳታ ከሚያስፈልገው የሰው ቁጥር አንፃር በሀገር ደረጃ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ጥቂት ናቸው፡፡ ይህ ማለት ተቋማቱ የያዙት የሰው ቁጥር ትንሽ ነው ብሏል። በየጎዳናው የወደቀው ሰው ደግሞ ብዙ ነውና ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ የሃይማኖት ተቋማትና መንግሥት በዚህ ዓይነት ሥራዎች ላይ በስፋት መሥራት የግድ የሚልበት ሁኔታ መኖሩን አስረድቷል፡፡

የተረጂው ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ከማኅበረሰቡም ሆነ ከመንግሥት ብሎም ከሕዝቡ ብዙ የሚጠበቅ መሆኑን በማስታወስ፤ ለበጎ ሥራዎች በእኔነት ስሜት መተጋገዝ እና መረዳዳት ከሁሉም የሰው ልጆች የሚጠበቅ የውዴታ ግዴታ እንደሆነም ያስረዳል። አሁን ላይ ባይሽ ኮልፌ ለአንዳንድ የሥራ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ የሚጠቀምበት ቢሮ እንጂ በቋሚነት አረጋዊያን የሚረዳበት ቦታ እንደሌለው የሚናገረው ወጣት ሄኖክ፤ «ማህበሩ ህልውና ኖሮት መቆየት እንዲችል እና የሄኖክም ሆነ የሌሎች መስራቾች ተሞክሮ እንዲሰፋ፤ ካለፍን በኋላም ማህበሩ ለብዙዎች ማረፊያ እንዲሆን ለማስቻል እየተሰራ ነው፡፡» ሲል ተነግሯል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አሁን ላይ የባይሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ማህበር ትልቁ ዓላማ ለማህበሩ ቋሚ የሆነ ቦታ እንዲኖረው ማስቻል ነው የሚለው ሄኖክ፤ ለዚህም እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል፤ ይህንኑ ዓላማ ከመልካም ነገር ጋር ለመተባበር ሁልጊዜም ከማይሰንፉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር እውን ለማድረግ እየሰሩ እንደሆነ ተነግሯል።

የ2014 ዓ.ም የዓመቱ የበጎ ሰው እጩ ተሸላሚ የነበረው ወጣት ሄኖክ፤ ለሚያከናውነው የበጎ አድራጎት ሥራ ከተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች ዕውቅና የተሰጠው ቢሆንም፤ የተሰጡት ዕውቅናዎች ተጨማሪ የቤት ሥራ ይዘው የሚመጡ እንጂ ባለበት እንዲቆም የሚያደርጉ አለመሆናቸውንም ይናገራል።

በጎነት ሽልማት የሚያሻው ባይሆንም፤ ከብዙ ሰው መካከል ከአንድ እስከ ሶስት ውስጥ መግባት በራሱ የሚሰጠው ትርጉም የሰው ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ ማሳያ ነው የሚለው ወጣት ሄኖክ፤ ይህ ለእርሱ እንደ ሸክምም ብዙ የቤት ሥራ የመስጠት ያህል መሆኑን ይናገራል፡፡ «የሚሰማኝ ከአንተ ብዙ እንጠብቃለን የማለት የአደራ ምልክት እንደሆነ ነው» የሚለው ወጣቱ፤ «በሠራሁት ሥራ ስለሚገባኝ የተሰጠኝ ሽልማት ነው ብዬ አላምንም፤ ምን ሰርቼ ነው ብዬ አስባለሁ ለተሰጠኝ ዕውቅና፣ ሽልማትና ፍቅር ግን ትልቅ ክብር አለኝ፡፡ ዕውቅናውም ከሁሉም የባይሽ ኮልፌ አባላት ጋር በጋራ ያገኘነው ነው። ይህ መሆኑ ማኅበራችንን የሚያበረታታ ነው» ይላል።

ባይሽ ኮልፌ የብዙ ሰው የጠብታ ውጤት ነው የሚለው ወጣት ሄኖክ፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ አብረውኝ ለነበሩ ድጋፍ ከማድረግ እጃቸው ያልተሰበሰበ ብዙ ደግ ልቦች አሉና ያገኘው ዕውቅና ለእነዚህ ለመልካምነት ለተዘረጉ እጆች ሁሉ የተሰጠ ማበረታቻ እንደሆነ ነው ሲል ይናገራል።

የዚህ የመልካም ተግባር ባለቤት የሆኑት ወጣቶች የሚያከናውኑት ማኅበረሰብ ተኮር የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ነው፡፡ ስለሆነም ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ለአረጋውያን፣ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች አቅማቸው በፈቀደ መጠን የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስልቶችን በመጠቀም እንደ ልብስ፣ ምግብና መሰል መሠረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት ጀምሮ ሌሎች ድጋፎችን ስለማድረጋቸው ወጣቱ ይገልፃል።

ወጣት ሄኖክ እንደሚናገረው፤ ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከመስጠታቸው በተጨማሪ አሁን በሀገራችን ላይ ያለው የሰላም እጦት መፍትሔ እንዲያገኝ ግንባር ቀደም ተዋናይ በመሆን ሚናቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ ከእነዚህ ሚናዎች መካከል በዋናነት ከበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ በተጓዳኝ በማኅበራዊ ሚዲያ ድህረ ገፆች አማካኝነት ሰላም ጠፍቶ ግጭት፣ ልማት ጠፍቶ ጥፋት፣ እድገት ሳይሆን ውድቀት እንዲነግስ ለማድረግ ብሔርን ከብሔር፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት በማጋጨት የሀገርን ሰላም የዜጎችን ወጥቶ መግባት አደጋ ላይ ለመጣል የሚጥሩ ኃይሎችን መላ ሊባል ይገባል ይላል።

ወጣት ሄኖክ እንደሚገልጸው፤ በባይሽ ኮልፌ የ13 ዓመታት ጉዞ ባላቸው ነገር ሁሉ ከጎን የሚቆሙ ጥቂቶች እንዳልሆኑ ይናገራል። ሕሙማን ላይ ለውጥ ሲታይ ደግሞ ያሉት ለውጦች አስደሳች እና ተስፋ አጫሪ ስለሚሆኑ የሌለውንም መዳን በመመኘት መንቀሳቀስ ይመጣል ይህ ደግሞ ጥንካሬ የሚሰጥ ነገር ነው ይላል። በሕመም ውስጥ የነበሩ ሰዎች ተሽሏቸው ከራሳቸው አልፈው ለሰው ማሰብ እና መጨነቅ ሲጀምሩ ማየት፣ ትናንት ጎዳና ላይ ወድቀው የነበሩ ሰዎች ለሌላ ለመትረፍ ጥረት ሲያደርጉ ሲመለከት ልቡ እንደሚነካ እና ጎዳና ላይ ወድቆ ያለ ሰው ሁሉ ድኖ ማየት ምኞቱ መሆኑን ይናገራል፡፡

በሚያገግሙ ሰዎች ላይ ያለው ለውጥ ለሌሎችም ለመድረስ በሚደረገው ጥረት ስንቅ ሆኖ እንደሚያገለግለው የተናገረው ወጣት ሄኖክ፤ ይህም በሥራው እንዲቀጥል እና እንዲበረታታ ሌሎች ሰዎችም ዓላማውን እንዲከተሉ ያደረገው መሆኑን ወጣት ሄኖክ ይናገራል።

በጎነት ዓይነቱ የበዛና አከናወኑም የተለያየ ነው የሚለው ሄኖክ፤ ሀገር ማለት ሰው እንደመሆኑ ሀገር የሚለውጥ መልካም ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች ሀገራቸውን ለማቅናት በበጎ አድራጎት ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡ የወጣትነት ትኩስ ጉልበት ለበጎነት ሲውል ደግሞ እንደ ሀገር ትርጉሙ ብዙ እንደሆነ ይናገራል።

ለመልካም ሥራ ረፍዶ አያውቅም የሚለው ሄኖክ፤ በጎነትን ዛሬ መጀመር ይቻላል። ካለን ነገር ለማካፈል የግድ ሀብታም መሆን ወይም ሚሊየነር መሆን አያስፈልገንም፤ ማንኛውም ሰው በጎ ነገር ማድረግ ይችላል። ስለዚህ የወደቁትን ለማንሳትና ጠያቂና አጋዥ የሌላቸውን ሰዎች አለንላችሁ ለማለት ሁሉም ሰው በተለይ ወጣቱ እጁን መዘርጋት እንዳለበት ይናገራል።

በመጨረሻም ሄኖክ ባስተላለፈው መልዕክት፤ ባይሽ ኮልፌ እስከ አሁን በቆየባቸው 13 ዓመታት ውስጥ ጫማ ከመጥረግ፣ ሶፍትና ቁልፍ መያዣ ፀሐይ ወይም ብርድ ነው ሳይሉ ሁልጊዜም ከማህበሩ ጋር አብረው ለነበሩ፣ ከዚህ በተጨማሪ በውጭ ሀገር በስደት ላይ ሆነው ስለ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ግድ ብሏቸው ለሚጨነቁ ድጋፍ በማድረግ ከማህበሩ ጎን ለቆሙ በጎ ፈቃደኛ የባይሽ ኮልፌ አባላት በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናን ማቅረብ እንደሚፈልግ ተናግሯል።

# የምድር በረከት

## ደቡብ ኢትዮጵያ- የማዕድን ምርት ቅኝት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገ ክልል ነው። በክልሉ ከፍተኛ ክምችት ያለው የማዕድናት ሀብቶች ይገኙበታል። ከእነዚህም ውስጥ የድንጋይ ከሰል፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን እና የመሳሳሉ በርካታ ማዕድናት የሚገኙበት ክልል ነው። ክልሉ በተለይ በድንጋይ ከሰልና በከበሩት ማዕድናት ልማት ተጠቃሽ ነው።

በክልሉ የማዕድን ዘርፉ የማዕድን ሀብት በጥናት ተለይተው እየተሠራባቸው እንዳሉ ሁሉ በጥናት ያልተለዩም በርካታ ማዕድናት ያሉበት ነው። እነዚህን በማዕድናት በማልማት ረገድም በርካታ አምራቾች ፍቃድ ወስደው ወደ ልማት ሥራ መግባታቸው የክልሉ መረጃ ያመላክታል።

የደቡብ ኢትዮጵያ የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የማዕድንና ኢነርጂ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ኦላዶ ኦሎ በክልሉ በርካታ የማዕድን ሀብቶች ያሉ መሆኑን ይናገራሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ በክልሉ በጥናት የተለዩና ያልተለዩ ማዕድናት አሉ። ከእነዚህ ውስጥ የኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ የኮንስትራክሽን፣ የከበሩ ማዕድናት እና ብረትና ብረት ነክ ማዕድናት ተጠቃሾች ናቸው። የድንጋይ ከሰል፣ የቪንቶናይት ፣ የዲያቶማይት እና የመሳሰሉ የከበሩ ማዕድናት ክምችት መኖሩ በጥናት ተለይቷል።

«ክልሉ በዋናነት በድንጋይ ከሰል እና የከበሩ ማዕድናት ላይ እየሰራ ነው» ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በተለይ የድንጋይ ከሰል፣ ቪንቶናይት እና ዲያቶማይት በጥናት የተለዩና በቡርጂና በጌዲዮ ዞን መኖራቸው የተረጋገጠ ነው ይላሉ። ሌሎች የማዕድን ዓይነቶች ደግሞ ልማቱ ላይ የሚሳተፈው ባለሀብት በራሱ አጥንቶ ወደ ሥራ የሚገባባቸው መሆናቸው ጠቅሰው፤ በዚያ መሠረት ለማልማት ለሚፈልጉ አካላት ክልሉ ፈቃድ እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

እንደ ምክትል ኃላፊው ገለፃ፤ የድንጋይ ከሰልና የከበሩ ማዕድናት በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሲሆን፤ ጎሞ፣ ወላይታ፣ ጎራዱላ፣ ቡርጂ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጌዶዮ ፣ ኮንሶ እና ጎፋ ይገኛሉ። እነዚህን ማዕድናት ለማምረት በአነስተኛ ደረጃ የተደራጁ ማህበራትና ኩባንያ ደረጃ ፍቃድ የወሰዱ 123 አምራቾች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አሁን ላይ ወደ ማምረት ገብተው እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉት 22 ያህሉ መሆናቸው ጠቁመዋል።

በተያዘው (በ2016) በጀት ዓመት ከማዕድን ዘርፉ 56 ሚሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው የሚሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊ፤ በሩብ ዓመቱ ብቻ 14 ሚሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ፤ 13 ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘት መቻሉን ተናግረዋል። ይህም አፈጻጸሙን የእቅዱን 95 በመቶ እንዲሆን አድርጓታል ይላሉ። ከማዕድን ዘርፉ ከሮያሊቲ ክፍያም እንዲሁ በተያዘው በጀት ዓመት 43 ሚሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ በሩብ ዓመቱ 12 ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘት መቻሉን አመላክተዋል።

"የማዕድን ዘርፉ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር የሚችል ነው" የሚሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊ፤ በተያዘው በበጀት ዓመት ለ8ሺ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር የታቀደ ሲሆን፤ በሩብ ዓመቱ ለ878 ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ገልጸዋል።

በክልሉ ማዕድን ልማት ዙሪያ ላይ በርከት ያሉ ተግዳሮቶች እንዳሉ የሚገልጹት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከእነዚህም መካከል የአካባቢ ወጣቶች ሰፊ ኢንቨስትመንት በሚጠይቀው የማዕድን ሥራ ፈቃድ ተሰጥቶአቸው ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ በአልሚዎች ላይ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ መሆኑ ያነሳሉ። ይህንን ተግዳሮት ለመፍታትም ወጣቶችን ከአልሚዎች ከሚገኘው የወጣቶች ፈንድ በሚል ልዩ መመሪያ እንዲወጣ በማድረግ ፈንዱን ወጣቶቹ በሚፈልጉት የሥራ ዘርፍ እንዲንቀሳቀሱበት በሚመለከታቸው አካላት አስተባባሪነት ተግባራዊ ለማድረግ የመመሪያውን የማጽደቅ ሥራ መሥራቱ አስታውቀዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የኮንስትራክሽን ማዕድን አምራቾች የገበያ ችግር መኖሩን ጠቅሰው፤ ይህም በነፃ ተጠቃሚነት ሽፋን ምርቱን እያወጡ የሚሸጡ



አቶ ኦላዶ ኦሎ

**በተለይ የድንጋይ ከሰል በክልሉ ያለው ብቻ ሳይሆን በሀገር ውስጥ ያለው የድንጋይ ከሰል ላይ በጂኦሎጂካል ሰርቬይ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የኢነርጂ ይዘቱ ከውጭ ከሚገባው በብዙ የሚተናነስ አይደለም። ጥሩ ይዘት ያላቸው የድንጋይ ከሰል ዓይነቶች አሉ**

በፌዴራል ደረጃ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በሚሰሩ አንዳንድ ኮንትራክተሮች የሚስተዋል በመሆኑ አመላክተዋል። ለዚህም ስለተወሰደው የመፍትሔ ርምጃ መኖሩን ጠቅሰው፤ በነፃ ተጠቃሚነት ስም የኮንስትራክሽን ማዕድንን ለግል ጥቅም የሚያውሉ አካላትን በተመለከተ ለወረዳ አመራሮች ተገቢውን ግንዛቤ የመፍጠርና የማዕድን ዘርፍ መዋቅሩ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርግ አቅጣጫ በማስቀመጥ እግሩን ለመፍታት እየተሞከረ እንደሆነ ነው ምክትል ኃላፊው ያስረዱት፡

ለውጭ ምንዛሪ ጠቃሚ የሆኑ የጌጣጌጥ የከበሩ ማዕድናት በክልሉ የሚገኙ ቢሆንም ከመሠረተ-ልማት እና ከማምረቻ ቴክኖሎጂ ውስንነት የተነሳ በሙሉ አቅም አምርቶ ለመጠቀም ያለመቻሉም አንስተው፤ ይህን ተግዳሮት ለመቅረፍ አቅም ያላቸው ባለሀብቶችን ከጌጣጌጥ ማዕድን አምራቾች ጋር እንዲቀናጁ በማድረግ ምርቱ እንዲወጣ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል ምክትል ቢሮ ኃላፊው በተግዳሮትነት የሚነሳው ለሀገር ውስጥ አልሚዎች የኢንዱስትሪ ማዕድን ፈቃድ የመስጠት ሥልጣኑ የክልሎች ሆኖ ሳለ በፌዴራል ማመልከቻዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ በሚደረገው እንቅስቃሴ ክልሎች አልሚዎቹን ተቀብለው ለማስተናገድ አስቸጋሪ እንዳደረገው ገልጸዋል። ለዚህም ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር በክልል ሊስተናገዱ የሚገባቸውን ክልሉ እንዲያስተናግድ ማድረግ እንዳለባቸው በደብዳቤ የማሳወቅ ሥራ እንደተሰራ ይገልጻሉ።

የድንጋይ ከሰል አምራቾች በቀጥታ ለፋብሪካዎች የማቅረብ እድል ባለማግኘታቸው በመሃል ያሉ በአቅራቢነት ስም የሚታወቁ ከፋብሪካዎች ጋር ውል እየገቡ ምርቱ የሚሄድ በመሆኑ ከማዕድን ምርት ሽያጭ ክልሉ የሚያገኘው ገቢው ዝቅትኛ እንዲሆን አድርጎታል ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ የድንጋይ ከሰል የሚመረትበት ወረዳ ከሮያሊቲ የሚያገኘውን ገቢ ለጊዜው በፋብሪካ ሽያጭ ዋጋ እንዲሰበስብ በክልሉ በኩል አቅጣጫ ተቀምጦ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝም አስረድተዋል።

«በክልሉ ሰላም የሰፈነበት መሆኑ እንዲሁም ያለው ሰፊ የሰው ኃይል ለማዕድን ልማቱ መልካም አጋጣሚን የሚፈጥሩ ናቸው» የሚሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በክልሉ ማዕድናት በማምረት ረገድ ኩባንያዎችና አነስተኛ አምራች ማህበራት ተደራጅተው የሚሰሩ እንደሆነ ይናገራሉ። በተለይ በከበሩት ማዕድናት ላይ በማህበር ተደራጅተው የሚሰሩ አምራቾች መኖራቸው ጠቅሰው፤ በከበሩ ማዕድናት አምራቾች ትስስር ስላልተፈጠረላቸው በቂ ገበያ ስለማያገኙ በችግር እንደሚፈተኑ ይገልጻሉ።

የከበሩ ማዕድናት ላይ የሚነሳው የገበያ ትስስር ችግር እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ በሕገ ወጥነትም እንደሚጠቁሙ አመላክተዋል። የከበሩ ማዕድናት በቀላሉ ማዘዋወር ስለሚቻል የከበሩት ማዕድናት በሕገ ወጥ መንገድ ስለሚወጡ ያለው የገበያ ትስስር የላላ እንዲሆን እንዳደረገውም አስረድተዋል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊው እንደሚሉት፤ የከበሩ ማዕድናት የሚያመርቱና የሚያዘዋወሩ ሕጋዊ ፍቃድ ያገኙ አምራቾች አሉ። አሁን ላይ ችግሩ ጎልቶ የሚታየው ታችኛ መዋቅር በወረዳ ላይ የሚገኝ ነው። በክልሉ እስከታች ያሉ መዋቅር ድረስ ወርዶ ግንዛቤን የማስፋት ሥራ እየተሰራ ነው። በሕገወጦች ላይም ርምጃ ለመውሰድ ከጸጥታ አካላት ጋር በመሆን ሥራዎች እየሰሩ መሆኑን ያስረዳሉ።

"በከበሩ ማዕድናት ልማት ላይ አንዳንዶቹ ፍቃድ ያላቸው አካላት ቢሆን የሚሰሩት ሕጋዊ የአሠራር ሥርዓትን ተከትለው አይደለም" የሚሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ እነዚህም ቢሆን ሕጉ በሚፈቅድላቸው አሠራር መሠረት መሥራት እንዲችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሰራ እንደሆነ ይገልጻሉ። ከዚህ በተጨማሪ ከወረዳዎች በሚላከው ሪፖርት መሠረት በሕገ ወጥነት መንገድ ማዕድናት ሲያዘዋወሩ የተገኙት ላይ ሕጋዊ ርምጃ እንደተወሰደ እንደሆነም አስታውቀዋል።

በድንጋይ ከሰል አምራቾች ላይ ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች ጋር የገበያ ትስስር ስለፈጠሩ እምብዛም የገበያ ትስስር ችግር አይስተዋልም። ነገር ግን በድንጋይ ከሰል ላይ የሚነሱ የጥራት ችግሮች እንዳሉ የጠቆሙት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከጥራት አንጻር የሚነሱ ሁለት ዓይነት ችግሮች መሆናቸው ይገልጻሉ። አንደኛው ከአመራረት ዘዴ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የጥራት ጉድለት ችግር ነው። በዘልማድና በባሕላዊ መንገድ የሚያመርት መሆኑና ማዕድናቱ ሲያወጡ ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር የሚቀላቀልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ጠቅሰው፤ ይህንን ችግር ለመፍታትም የአመራረት ዘዴን በመቀየር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዲመረቱ እየተደረገ እንደሆነም አመላክተዋል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰልን የሚጠቀሙት ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ የተመረተውን የድንጋይ ከሰል ምርት የጥራት ጉድለት አለው በማለት ከውጭ ለማስገባት የመሞከር ነገር ይስተዋላል ይላሉ። መንግሥትም በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ከውጭ የሚመጣው የድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ ምርት እንዲተካ የማድረግ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ቢሆንም እነዚህ ፋብሪካዎች ግን የመቀበል ፍላጎታቸው በጣም አነስተኛ ነው ሲሉም ያነሳሉ።

ለዚህም ፋብሪካዎቹ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት ጥራት እንደሆነ ጠቅሰው፤ ነገር ግን ጥራት ላይ በደንብ ከተሰራ የውጭ ምንዛሬ ማዳን የሚቻልበት እድል መኖሩን ይገልፃሉ።

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ሃሳብ፤ በተለይ የድንጋይ ከሰል በክልሉ ያለው ብቻ ሳይሆን በሀገር ውስጥ ያለው የድንጋይ ከሰል ላይ በጂኦሎጂካል ሰርቬይ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የኢነርጂ ይዘቱ ከውጭ ከሚገባው በብዙ የሚተናነስ አይደለም። ጥሩ ይዘት ያላቸው የድንጋይ ከሰል ዓይነቶች አሉ። ይህ ሆኖ ሳለ በፋብሪካዎቹ ጥራት ላይ የሚቀርበው ቅሬታ የሀገር ውስጥ የሚመረተው ጥራት ችግር ኖሮት ሳይሆን የፋብሪካዎች ፍላጎት ውጭ የማስገባቱ ላይ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ መገደዳቸውን ነው ያስረዱት።

"በክልሉ የድንጋይ ከሰል ለማልማት 43 የሚሆኑ አምራቶች ፍቃድ ወስደው ልማቱ ላይ ተሰማርተዋል" ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከእነዚህ ውስጥ ግን አሁን ላይ ጥሩ የሚባል እንቅስቃሴ በማድረግ የማምረት ሂደት ላይ ያሉ 12 ያህሉ እንደሆነ ይናገራሉ። የተቀሩት ግን እስካሁን ወደ ማምረት ያልገቡ ሲሆን ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በክልሉ በዘርፍ ላይ ተሰማርተው ማዕድናት ለማምረት ፍቃድ የወሰዱት ሆነ በምርመራ ሂደት ላይ ያሉት በርካታ አምራቾች መኖራቸው ጠቅሰው፤ ቁጥራቸው ብዙ ከመሆኑ በላይ ተበታትነው በየራሳቸው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ሂደቱ ከባድ አድርጎታል ይላሉ። እነዚህ ውስጥ የተወሰኑቱ በአንድ ላይ በጋራ ሆነው ቢሰሩ የተሻለ ማምረት የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ አንስተው፤ በቀጣይም አንድ ላይ ሰብሰብ ብለው ትልቅ አቅም ፈጥረው ወደ ልማቱ ቢገቡ የተሻለ እንደሚሆን ለማስገንዘብ እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል።

ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ከባለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል። የማዕድን ዘርፉ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጠባቸው አምስት ዘርፎች መካከል አንዱ ነው። ይሄ ርምጃ እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የሚቆጠር ነው። ሌላው ሰፊ የሰው ኃይል እና በተለይ ወጣቱ ኃይል መኖሩ ሌላኛው ትልቅ አቅምን የሚፈጥር ነው። በመሆኑም ባለሀብቱን ከሰው ኃይሉ ጋር በማስተሳሰር በዘርፉ እንዲሰማሩ ማድረግ ይቻላል።

"ክልሉ በአንጻራዊነት ሰላምና መረጋጋት የሰፈነበት ክልል ነው" ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ ሕዝቡም ልማትን የተጠማ ስለሆነ በማዕድን ዘርፉ ልማት ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ አልሚ ባለሀብቶችም ሆነ ግለሰቦች ወደ ክልሉ መጥተው መሥራት እንደሚችሉ ይገልጻሉ። ለዚህም ደግሞ ክልሉ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍና ትብብር የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰው፤ የማዕድን ዘርፉ ላይ ኢንቪስት ማድረግ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

# ጥቁር ና ነጭ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

እማማ ሸጌ ሰፈሩ ውስጥ የታወቁ አረቄ ነጋዴ ናቸው። ከእጃቸው ላይ ማንቆርቆሪያ፤ ከፊታቸው ላይ ፈገግታ ጠፍቶ አያውቅም። ቀይ ናቸው፣ በቀይ መልካቸው ላይ ተመዞ የወጣው አፍንጫቸው ማንም ሳያየው ዓይን ውስጥ ይገባል። እንደ ቀለበት መንገድ አንገታቸው ላይ የተጥመለመለው ንቅሳት በነጭ ብራና ላይ የተነደፈ ሥዕል ይመስላል። ከወገባቸው ጠፍቶ የማያውቀው መቀነት በሀገር ባንዲራ ተሸልሞ ሲታይ ሀገር ወዳድነታቸውን ያሳብቃል። እማማ ሸጌ በሁለት ነገር አይታሙም፤ አንደኛው ቁጥር ነው . . . የትኛውም ጠጪ ምንም ያክል ቢጠጣ ከእማማ ሸጌ ስሌት አያመልጥም። በጓዳ ጎድጓዳው እየተዋከቡ ጭንቅላታቸው ግን የእያንዳንዱን ጠጪ መለኪያ ይቆጥራል። ሁለተኛው ደግሞ ፍራንክ ነው . . . እማማ ሸጌን ከማታለል ከጆ ባይደን ቢሮ መረጃ መስረቅ ይቀላል። የአንድ ጠጪን ሂሳብ ለማስላት ምንም አይነት የቴክኖሎጂ ውጤት አይጠቀሙም፤ ለጥቂት ደቂቃ ዝም በማለት በጭንቅላታቸው ካወጡ፣ ካወረዱ በኋላ የማይጠጋጋ ሂሳብ ይነግሩሀል። ይሄ ልዩ ብቃታቸው ነው። የሚገርመው ደግሞ ምንም አይነት የትምህርት ደረጃ የሌላቸው መሆናቸው ነው። በሦስት መንግሥት ላይ ተረማምደው መጥተው እንኳን ለሀገሬ ሕዝብ ባለውለታ ለሆነው መሠረተ ትምህርት ባይተዋር ናቸው። የጭንቅላታቸው "አይኪው" (ችሎታ) መዛኝ ቢያገኝ ኖሮ በሂሳብ ስሌት አቻ የሌላቸው እድሜ ጠገቧ አዛውንት በሆኑ ነበር።

አስረሳህኝ የእማማ ሸጌ የረጅም ጊዜ የአረቄ ደንበኛ ነው። አስረሳህኝን ከሌሎቹ ጠጪዎች ለየት የሚያደርገው አረቄን እንደ ውሀ መጠጣቱና ራዕይ ያለው ሰካራም መሆኑ ነው። አረቄ ሲጠጣ ዓለም ላይ ጣፋጩን መጠጥ የሚጠጣ ነው የሚመስለው። አያቃጥለው፤ አይጎረብጠው፤ በቃ አንስቶ ኸው . . . ምጥጥ፣ ሽምጥጥ። ከእማማ ሸጌ ቤት ሌላ ሕይወት ያለ አይመስለውም። እማማ ሸጌ እግዜሩ ናቸው . . . ምንም ፈልጎ የማያጣባቸው፤ ከእሳቸው ውጪ እስትንፋስ የሌለው ይመስል ውሎና አዳሩ እዛው ነው። ሰፈር ሲለቁ ሰፈር እየለቀቀ፤ ሀገር ሲለቁ ሀገር እየለቀቀ በሄዱበት በመሄድ ዛሬም ድረስ ምርጥ ደንበኛነቱን አስመስክሯል። ከወገቡ ጎበጥ ያለ ነው። እድሜ ግሳንግሱን ጭኖበት ወደ መሬት ጎንበስ ያለ . . .። በግንባሩ ሜዳ ላይ ዘመን ያሰመራቸው ቀጫጭን መስመሮች ይታያሉ። በዘመን የተኳሉ . . . በጊዜ የተቀለሙ አለላ መልኮች።

የአስረሳህኝ ሌላው ስሙ ባለራዕዩ ነው። በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ከመጠሪያ ስሙ በላይ በዚህ ስሙ ይታወቃል። አስረሳህኝና ራዕይ ተነጣጥለው የማይታዩ፣ የአንድ እጅ መዳፍና አይበሉባ ናቸው። ገና እግሩ ደፍ ሳይረግጥ ቀድመውት የመጡት የአረቄ ቤት ወዳጆቹ ባለራዕዩ ሲሉ በጭብጨባ ይቀበሉታል። ያልኖረው፣ ወደ ፊት እኖረዋለሁ ብሎ የሚያስበው ሕልም አለው። እውነት ለመናገር እየኖረው ያለውን ሕይወቱን አይወደውም። አረቄ ቤት ከመዋልና ሰክሮ የትም ወድቆ ከማደር ባለፈ ለዚች ዓለም ያበረከተው አስተዋፅዖ የለም። በዚህ ይበሳጫል . . . ነገ ላይ ሌላ ሰው ሆኖ ራሱን ማየት ይፈልጋል። ከዚህ የበዛ እምነቱ በመነሳት ጓደኞቹ ባለራዕዩ አሉት . . . ባለራዕዩ ሆኖ ቀረ። ሕልሙ የሚጀምረው ግን እማማ ሸጌ ቤት ሲደርስና አንድ ሁለት መለኪያ አረቄ ሲደረግም ነው። ከዛ በኋላ ሌላ ነው . . . ባለቢጫ አይኖቹ ጓደኞቹ በወሬው እስኪሰለቹ ድረስ ስለ ሕልሙ ይዘባርቃል።

እማማ ሸጌ ከነማንቆርቆሪያቸውና ከነፈገግታቸው ከእቃ ቤቱና ከሳሎኑ አዋሳኝ ላይ ቆመው መለኪያው የጎደለበትን ይቃኛሉ። በዚህ መሐል ጎጃም አዘነ የለበሰ አንድ አዙሮ አደር "ሎተሪ . . . ነገ የሚወጣ . . . አስር ሚሊዮን ብር" እያለ ወደ ውስጥ ገባ።

አስረሳህኝ የሎተሪ አዟሪውን እጅ አፈፍ አድርጎ ... "አ . . አን . . ንድ ስጠኝኝኝ" አለው . . . ስካር ባነቀው ንግግር። እጁን ሱሪው ኪስ ከቶ ፍራንክ ሊያወጣ እየተፍጨረጨረ። ባለሎተሪው ከትከሻው የተንሸራተተ ጎጃም አዘነውን ሽቅብ እያጣፋ እንደተባለው አንድ በጥሶ ሰጠው።

አስረሳህኝ ሎተሪውን አፍጦ እየተመለከተ "እድለ ቢስ ነኝ፤ ግን ደግሞ ባለራዕይ . . ያልተኖረ፣ ያልተነካ ድንግል ራዕይ። " አለ ለራሱ።

ከቀናት በኋላ አስረሳህኝ እማማ ሸጌ ቤት አምሽቶ ሰክሮ ቤቱ ሲገባ ጠዋት የከፈተው ሬዲዮ እያወራ ያገኘዋል። ጫማውን ሊያወልቅ ሲንደፋደፍ ሬዲዮው የምሽቱን የሎተሪ አሸናፊ ቁጥር ሲናገር አንድ ሆነ። እጁን ወደ ኪሱ ከቶ ሎተሪውን አወጣ . . .። የሰዓቱ ዜና አንባቢ የመጀመሪያውን ቁጥር ተናገረ፤ አስረሳህኝ እጅ ላይ ካለው የሎተሪ ቁጥር ጋር ተመሳሳይ ነበር። አስረሳህኝ አላመነም . . . ስካሩ ለቀቀው።

ዜና አንባቢው ቀጥሎ ያለውን ተናገረ . . . አሁንም ተመሳሰለ። ሰካራሙ ሰው እየሆነ ያለውን ነገር ማመን አልቻለም። በዜና አንባቢው አፍ ያልተጠሩ የመጨረሻ አራት ቁጥሮች ይቀራሉ። አስረሳህኝ ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም።

በመሐል ሬዲዮኑ ቀጠለ . . . የአስረሳህኝን የሎተሪ ቁጥር እያየ የሚናገር ይመስል ቁጥሩ ከቁጥሩ ጋር አንድ ሆነ። አስረሳህኝ ሳያስበው ጮኸ። ከዚህ በኋላ የሆነውን አያስታውሰውም . . .። የመጨረሻ ሁለት ቁጥሮች ይቀሩታል። ከነዚህ ሁለት ቁጥሮች በኋላ የአስረሳህኝ ታሪክ ይቀየራል። ዜና አንባቢው ገና አልጠራቸውም . . . ልቡ ድም . . . ድም አለ።

ከሁለቱ አንዷ በዜና አንባቢው አፍ ተጠራች። በደስታ ውስጥ ሆኖ አንዷን ሰማት . . . እሱ እጅ ላይ ካለችው ጋር ተመሳሳይ ነበረች። አስረሳህኝ ደስታ አሸነፈው . . . የመጨረሻዋን ቁጥር ሳይሰማት በደስታ መሬት ላይ ተዘረረ።

ሌሊት ሲነጋጋ አስረሳህኝ ራሱን ከሳተበት ነቃ። ምን ተከስቶ እንደነበር ለማስታወስ አልተቸገረም። እስኪነጋ በደንብ አሰበ። እማማ ሸጌ አረቄ ቤት ላይደርስ፤ መርካቶ ጠጅ ቤት ላይገባ፤ ሰባተኛ ጉሮኖ ውስጥ ላይገኝ፤ መዋያውን ዱባይና ሙባይ ከቆነጃጅት ጋር ሊያደርግ ከወዲሁ አሰበ። ሌሊቱ ራቀበት. . . ንጋት ተሰወረበት። ነግቶ እየመሸ እንጂ መሽቶ እየነጋ፤ ሰዓቱም ወደ ኋላ እንጂ ወደ ፊት የሚቆጥር አልመስልህ አለው።

12 ሰዓት ላይ ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ሄደ . . . የሥራ ሰዓት እስኪደርስ እየተንቆራጠጠ መጠበቅ ግድ ነበረበት።

"ምን ልርዳህ?" አሁንም አሁንም መነጽሩን ወደ ቅንድቡ የሚገፋ ሰው ጠየቀው።

"አስረሳህኝ እባላለሁ . . . እ . . ." አስረሳህኝ ያልተጠየቀውን መለሰ።

"እኮ ምን ልርዳህ?" መነጽሩን እየገፋ በድጋሚ ጠየቀ።

"የሎተሪ አሸናፊ ሆኜ፣ አንደኛ እጣ ደርሶኝ፣ ገንዘቤን ልቀበል መምጣቴ ነው። " በታላቅ ጉራና መኩራራት መለሰ።

"ሎተሪውን ልታሳየኝ ትችላለህ?"

አስረሳህኝ በቅድሙ መኩራራት በእጁ ጨምድዶ የያዛትን የሎተሪ ትኬት ዘረጋለት። ዓለም ፊቱ ላይ ትታየዋለች . . . ተዘርግታ ልትቀበለው።

መነጽሩን ወደ አፍንጫው ካልገፋ ሕይወት ያለው የማይመስለው ሰውዬ የሎተሪውን ቁጥር በደንብ ካየ በኋላ አጠገቡ ያለውን ኮምፒውተር መጎርጎር ጀመረ።

አስረሳህኝ . . . ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ስላለው አስደናቂ ሕይወቱ በማሰብ ላይ ነበር።

"አቶ አስረሳህኝ . . ." ከኮምፒውተሩ ላይ ቀና ብሎ ጠራው።

አስረሳህኝ ከሀሳቡ ባኖ እየወጣ . . . "አዎ ነኝ . . . አስር ሚሊዮን ብር . . . አቤት . . . አቤት" እየዘላበደ ወደ ሰውዬው ተንደረደረ።

‹አዝናለሁ! ሎተሪው አልደረሰህም . . ."

አስረሳህኝ ነፍስ ላይ ረጅም ዝምታ ሰፈረ . . .

"የመጨረሻዋ አንድ ቁጥር የተለየች ናት" መነጽሩን ወደ አፍንጫው እየገፋ ተናገረ።

በአስረሳህኝ ገጽ ላይ ጀምበር ተሰወረች። ከተስፋው ምሥራቅ ላይ ጀምበር ጠለቀች። የፈገግታው፣ የጽናቱ፣ የሁሉ ነገሩ ፀሐይ ዳመነች። ከእምነቱ ጋር ተኳረፈ . . .

ወደ ኋላው መሬቱ ላይ ሲዘረር . . . ዳግም ላለመነሳት የማለ ይመስል ነበር።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ በሃውቲ ታጣቂዎች ላይ ወታደራዊ እርምጃ መውሰድ እንደምትጀምር አስጠነቀቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ በሃውቲ ታጣቂዎች ላይ ወታደራዊ እርምጃ መውሰድ እንደምትጀምር አስጠነቀቀች።

በቀይ ባሕር የሃውቲዎችን ጥቃት ለማስቆም የተቋቋመው የጋራ የባሕር ቅኝት ግብረኃይል ለየመኑ ቡድን የመጨረሻ ነው ያለውን ማስጠንቀቂያ አስተላልፏል።

በዚህ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ላይ አሜሪካ፣ አውስትራሊያ፣ ባሕሬን፣ ቤልጂየም፣ ካናዳ፣ ዴንማርክ፣ ጀርመን፣ ጣሊያን፣ ጃፓን፣ ኔዘርላንድስ፣ ኒውዝላንድ፣ ሲንጋፖርና ብሪታንያ ፊርማቸውን አኑረዋል።

ሀገራቱ የመንግሥታቱ ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት በሃውቲ ታጣቂዎች እና የፋይናንስ ድጋፍ በምታደርግላቸው ኢራን ላይ እርምጃ እንዲወስድም ጠይቀዋል ብሏል አሶሴትድ ፕሬስ በዘገባው።

ቡድኑ የሚፈጽመውን ሕገወጥ ተግባር እንዲያቆምና በቁጥጥር ስር ያዋላቸውን መርከቦች እንዲለቅ የጠየቁት ሀገራቱ፥ በቀይ ባሕር ደህንነት መናጋት ምክንያት በዓለም ምጣኔ ሃብት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ቡድኑ ኃላፊነቱን ይወስዳል ሲሉም ገልጸዋል።

ስማቸውን ያልጠቀሱ የባይደን አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣንም "በኢራን የሚደገፉት የሃውቲ ታጣቂዎች ከዚህ በኋላ ከአሜሪካና አጋሮቿ የማስጠንቀቂያ መልዕክት አይጠብቁ" ያሉ ሲሆን ቡድኑ ጥቃቱን ከቀጠለ ወታደራዊ እርምጃ ልንወስድ እንችላለን ብለዋል።

የአሜሪካው ባለሥልጣን በየመኑ ቡድን ላይ ሊወሰድ ስለሚችለው ወታደራዊ እርምጃ ዝርዝር መረጃን ከመስጠት ተቆጥበዋል።

እስራኤል በፍልስጤማውያን ላይ የምትፈጽመውን በደል ካላቆመች ጥቃቴ ይቀጥላል ያለው የሃውቲ



**የሃውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባሕር በሚጓዙ መርከቦች በጥቂቱ 23 ጥቃቶችን ፈጽመዋል ተብሏል**

ታጣቂ ቡድን ትናንት ያወጣው መግለጫ ግን ለሀገራቱ ማስጠንቀቂያ ቁብ አልሰጠውም።

ቡድኑ ከታኅሣሥ 19/2023 ወዲህ ከእስራኤል ጋር ግንኙነት አላቸው ባላቸው መርከቦች ላይ በጥቂቱ 23 ጥቃቶችን መፈጸሙ ተነግሯል።

ባለፈው ሳምንትም የሲንጋፖር ሰንደቅ የምታውለበልብ መርከብን ለማገት ሙከራ ሲያደርግ የአሜሪካ ሄሊኮፕተሮች ሦስት የቡድኑን ጀልባዎች ማስጠሙና 10 ሰዎች መሞታቸው ይታወሳል።

ሃውቲ በአሜሪካ የተፈጸመውን ጥቃት እንደሚበቀል መዛቱና በመርከቦች ላይ ያነጣጠሩት የጥቃት እርምጃዎች የጋዛው ጦርነት እስካልቆመ ድረስ ይቀጥላል ማለቱም ውጥረቱን እንዳናረው ነው።

አሜሪካና አስተባብራ ያሰለፈቻቸው 12 ሀገራት በቀጣይ ወታደራዊ እርምጃ የሚወስዱ ከሆነም ከጋዛ ተነስቶ ቤሩት የደረሰው ጦርነት ሰንዓ መግባቱ የሚቀር አይመስልም።

## ሩሲያና ዩክሬን የእስረኛ ልውውጥ አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ እኛ ዩክሬን ከ470 በላይ የጦርነት እስረኞችን ተለዋወጡ።

ዩክሬን በጦርነቱ ምክንያት በሩሲያ ታስረው የነበሩ 230 ዜጎቿ ተለቀው ወደ ዩክሬን መግባታቸውን ገልጻለች።

የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር በበኩሉ 248 እስረኞች መለቀቃቸውን ነው ያስታወቀው።

በቀጣይ ወር ሁለት ዓመት የሚደፍነው የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ በርካታ እስረኞች የተለቀቁበት ስምምነት እንዲደረስ ዓረብ ኤምሬትስ የማደራደሩን ሚና ተወጥታለች።



**ሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ከጀመሩ አንስቶ 49 ጊዜ የእስረኛ ልውውጥ አድርገዋል**

የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስኬታማውን የእስረኞች ልውውጥ አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፥ "የእስረኞች ልውውጡ ኤምሬትስ ከሩሲያ እና ዩክሬን ጋር የመሠረተችው ጠንካራ ወዳጅነት ማሳያ ነው" ብሏል።

ሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ከጀመሩ አንስቶ 49 ጊዜ የእስረኛ ልውውጥ ማድረጋቸውን የዩክሬን የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ገልጿል።

ሁለቱ ሀገራት ባለፉት ስድስት ወራት ግን የእስረኛ ልውውጥ አላደረጉም።

ሩሲያ የእስረኞች ልውውጡ በተደረገበት እለት በቤልጎርድ 12 የዩክሬን ሚሳኤሎችን እና ድሮኖችን መጣሏን ገልጻለች።

ኬቭ ባለፈው ሳምንት በድንበር ከተማዋ ቤልጎርድ ላይ በፈጸመችው ጥቃት ከ25 በላይ ሩሲያውያን መገደላቸውን ተከትሎ ሞስኮ የአፀፋ እርምጃ መውሰዷን ቀጥላለች።

በመዲናዋ እና በዩክሬን ሁለተኛዋ ግዙፍ ከተማ ካርኪቭ ያነጣጠሩት ጥቃቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ የተጠናከሩ ናቸው ተብሏል።

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በቤልጎሮዱ ጥቃት ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ሲጎበኙ የበቀል ዛቻ ካሰሙ በኋላ የሩሲያ የሚሳኤልና ድሮን ጥቃት መባባሱን አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

# ለገና ላሊበላ - ለጥምቀት ጎንደር እንገናኝ

**አሲ ሴሮ**

ኢትዮጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቅርሶች ባለቤት ነች። የተፈጥሮ ሀብቶቹ ከኤርታአሌ እስከ ዳሎል፣ ከራስ ዳሽን እስከ ታችኛው ኦሞ ሸለቆ ድረስ የተዘረጉ ናቸው። ከእነዚህም መካከል አስደናቂ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣ እንዲሁም የሰው ዘር መገኛ ሥፍራዎች ተካተውበታል።

ይህ ደግሞ ኢትዮጵያን ለቱሪስት መዳረሻነት ከሚያበቋት ነገሮች መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው። ኢትዮጵያ በዓለም ቅርስነት 16 ቅርሶችን በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር ነች። በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ግንባታዎች በስፋት በመከናወን ላይ ናቸው።

ሀገራዊ ለውጡ ዕውን ከሆነበት 2010 ጀምሮ የተፈጥሮ ሀብቶችን በማወቅ፣ በመለየት፣ በማልማትና በመጠቀም ረገድ እምርታዊ ለውጦች ታይተዋል። በአጠቃላይ ወቅቱ ለቱሪዝም ዘርፉ ትንሳኤ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ሃሳብ አፍላቂነት እና መሪነት ለዘርፉ የተሰጠው ልዩ ትኩረት የሚያበረታታ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገር እና ገበታ ለትውልድ በሚል ማዕቀፍ በሀገራችን የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በዘመናዊ መልክ እንዲለሙ እና ለቀረው ዓለም እንዲተዋወቁ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ወደ ሥራ ተገብቷል። መዲናችን አዲስ አበባን ጨምሮ በአራቱም ማዕዘናት ሀብቶችን በመለየትና በማልማት የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ እጅግ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል።

በገበታ ለሸገር የቱሪስት መዳረሻዎች ግንባታ የአንድነት፣ የወንድማማችት እና የእንጦጦ ፓርኮች ለአዲስ አበባ ድምቀት ሆነዋታል። ለወትሮው በቱሪስት መተላለፊያነት የምትታወቀው አዲስ አበባ የቱሪስቶች መቆያ የመሆን ዕድልም አግኝታለች። በገበታ ለሀገር ፕሮጀክትም የጎርጎራ፣ የኮይሻ እና የወንጪ የቱሪስት መዳረሻዎች ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዕድገት ተጨማሪ ዕድሎችን ፈጥረዋል።

ከእነዚሁ የቱሪዝም ሀብቶች በተጨማሪ ኃይማኖታዊ በዓላት የቱሪስቶችን ቀልብ የሚስቡ ናቸው። በተለይም ደግሞ በላሊበላ የሚከበረው የገና በዓልና በጎንደር የሚከበረው የጥምቀት በዓላት ልዩ ድባብ ያላቸውና በቱሪስቶችም ዘንድ በናፍቆት የሚጠበቁ ናቸው። ገና በላሊበላ ልዩ ድምቀት አለው። ላሊበላም በገና ልዩ ግርማ ሞገስ ታገኛለች። ይህንኑ በዓል ለማድመቅም እስከ 2 ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች በላሊበላ ይታደማሉ።

ገና የሚለው ቃል ከግሪክ ቋንቋ የተገኘ ሆኖ ትርጉሙም ልደት ማለት ነው። የክርስቶስ የልደት በዓል በመላው ዓለም በተለያዩ ሀገራት የሚከበር ሲሆን፣ የጎርጎሮስያኑን የዘመን አቆጣጠር በሚከተሉ ሀገራት ታኅሣሥ 16 (December 25) ይከበራል። ሌሎች ጥቂት ሀገራት ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ታኅሣሥ 29 ያከብሩታል። በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ እንደ ዘንድሮው ታኅሣሥ 28 ይውላል።

በዚህም ሕንድ፣ እስክንድርያ፣ ግብጽ፣ ሶሪያ እና አርመንያ የመሳሰሉት ከኢትዮጵያ ጋር በተመሳሳይ ቀን የገና በዓልን የሚያከብሩ ሀገሮች ናቸው።

በኢትዮጵያ የገና በዓል በየአካባቢው እና በየቤቱ የተለየ ድባብ ባለው መልኩ ቢከበርም የላሊበላን ያህል ግዝፈት ያለው አይደለም። ከላይ እንደገለጽነው በዓል አከባበር ሲነሳ ደግሞ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን አለማሰብ የሚቻል አይደለም።

ውቅር አብያተ-ክርስቲያናቱን በ13ኛው ክፍለ ዘመን የዛጉዌ ሥርወ-መንግሥት ንጉሠ ነገሥት የነበረው ላሊበላ ከአንድ ወጥ ቋጥኝ ጠርቦ የሠራቸው እንደሆነ ይታመናል። የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ቅዱስ ላሊበላ ከአስራ አንዱ የዛግዌ ሥርወ-መንግሥት ነገሥታት አንዱ ነው፣ ለአርባ ዓመት ከነገሡት ሰባቱ ውስጥም አንዱ ናቸው።

ንጉሥ ላሊበላ ለኃይማኖታዊ ጉዞ በተደጋጋሚ ወደ እየሩሳሌም ያቀኑ እንደነበር እና እየሩሳሌምን ንጉሥ ላሊበላ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኢትዮጵያውያንም መሳለም ይፈልጉ ስለነበር፣ በግብጽ በረሃ ይደርስባቸው የነበረውን ችግር ለማስቀረት የእየሩሳሌምን አምሳያ በኢትዮጵያ እንደተከሉ ይነገራል። በዚህም ንጉሥ ላሊበላ 11 ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት ያሳነጹ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ ቤተ-መድኃኔዓለም ከኹሉም ትልቁ እና 72 አዕማዳት ያሉት ነው።

ቤተ-ማርያም ደግሞ ንጉሡ አብዝተው ይወዱት የነበረና በቀን ለብዙ ጊዜ የሚመላለሱበት፣ ቤዛ ኩሉ ያሬዳዊ ዜማም የሚቀርብበት ነው ሲሉ ይገልጻሉ መምህሩ። ቀሪዎችም ቤተ-ደናግል፣ ቤተ-መስቀል፣ ቤተ-ደብረ ሲና፣ ቤተ-ጎለጎታ፣ ቤተ-አማኑኤል፣ ቤተ-አባ ሊባኖስ፣ ቤተ-መርቆሪዎስ፣ ቤተ-ገብርኤል ወሩፋኤል እና ቤተ-ጊዮርጊስ (ባለ መስቀል ቅርጹ) ናቸው።

በላሊበላ የገና በዓል ታኅሣሥ 29 (በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ታኅሣሥ 28) በልዩ ድምቀት ይከበራል። ዕለቱ ንጉሥ ላሊበላ የተወለዱበት ቀንም ነው። ቤዛ ኩሉ ተብሎ የሚጠራው ያሬዳዊ ዝማሬ ደግሞ በዚሁ በዓል የሚቀርብ ልዩ እና ታላቅ መንፈሳዊ ትዕይንት ነው። ዝማሬው የሚደረገውም ከቅዳሴ በኋላ በቤተ-ማርያም ነው።

ከታች ባለ ነጭ ካባ ካህናት፣ ከላይ ደግሞ ባለ ጥቁር ካባ ካህናት፣ እንዲሁም ዲያቆናትና ምዕመናን ተደርድረው በቅዱስ ያሬድ ዜማ ቤዛ ኩሉ እያሉ ይዘምራሉ። ይህም ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ በሰማይ መላዕክት፣ በምድር ደግሞ እረኞች (ሰብዕ) በአንድነት ሆነው መዘመራቸውን ለማሳየት መሆኑ ይነገራል።

ከዚህ የተነሳም በገና ሰሞን ላሊበላ መገኘት እንደ ዕድል የሚቆጠርና የሕይወት ዘመን ትዝታና ደስታ ሆኖ የሚዘልቅ መሆኑን በዓሉን የታደሙት ሰርክ የሚናገሩት ነው። ይህም ለገና ቀጠሮችን ላሊበላ ላይ እንድናደርግ ለማስቻል ከምክንያቶች በላይ ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ፣ ለዚህም ነው ቀጠሮችን ላሊበላ ላይ እንድናደርግ ማለቴ።

ሌላኛው ውብ ትዕይንትና ኢትዮጵያን በቱሪስቶች ዘንድ ተናፋቂ የሚያደርጋት በጎንደር የሚከበረው የጥምቀት በዓል ነው። ጥምቀት በጎንደር ልዩ ድባብ አለው። ኢትዮጵያ ዜና ጥምቀተ ክርስቶስን ከሰማችበት ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ በተለይም ከአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (6ኛው መ/ክ/ዘ) ወዲህ የጥምቀትን በዓል ዛሬ በሚታየው አኳኋን ስታከበር እንደ ቆየች የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

በክብረ በዓሉ ከመንበረ ክብራቸው ወጥተው ወደ ባሕረ ጥምቀት የሚወርዱት ታቦታት በካህናቱ ሃሌታ፣ በምእመናኑ እልልታ እና በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያኑ በተቋቋሙ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች መዝሙሮች ታጅበው በተመሳሳይ አኳኋን እንደሚመለሱ ይታወቃል።

በጥምቀት ዕለት የጎንደር አባቶችና እናቶች፣ ወጣቶችና ታዳጊዎች ባማረ የባህል ልብሶቻቸው ተውበው ደምቀው ጎንደርና ጥምቀትን ያደምቋታል አባቶች ጥንግ ድርብ እና አልፎ አልፎም ቀደምቱን ያማራ በርኖስ የባህል ልብሳቸውን ለብሰው ጥምቀትን ደምቀው ሲያደምቁት ፣ የቀረው ነዋሪም "ለጥምቀት ያልሆነ ልብስ ይበጣጠስ" ሆነና አቅሙ የፈቀደ አዲስ ልብስ አስርቶ ይለብሳል።

ወጣቶች አምረውና ደምቀው የሚታዩት በጥምቀት ነው። በጥምቀት የጎንደር ስመ ጥሩ የአርባ አራቱ ታቦት ፣ ሊቃውንት፣ ስመጥር የደብር አለቆችና ካህናት በሚያምረው ልብሰ ተክህኖ አምረውና ደምቀው ይታያሉ . . . በነጭ የባህል ልብሳቸው ላይ ጣል ከሚያደርጉት ጥቁር ካባቸውንና በራሳቸው ጥምጣም የሚታወቁት በጎንደር የቅኔ ፣ የመወድስና የአቋቋም ዝማሬ ሊቃውንት ባማረው አንደበታቸው የውዳሴ መዝሙር ጣዕመ ዜማ፣ ወርብና ሽብሸባውን በአደባባይ የሚያሰሙበት ልዩ አጋጣሚ ቢኖር ይህ የጥምቀት በዓል ነው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለችና በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ስንሄድ ያልተነኩ እምቅ ሀብቶች በስፋት የሚገኙባት ሀገር ነች። እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ ከታወቁ፣ ከለሙ እና ተገቢው ጥበቃ ከተደረገላቸው የኢትዮጵያ የብልጽግና እና የሕዝቦቿ የኑሮ መሠረቶች እንደሚሆኑ ይታመናል። ለዚህም ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በጅማና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶችን ሲጎበኙ ባስተላለፉት መልዕክት «ሀገሩን ያላወቀና ሀብቱን በአግባቡ ያልተጠቀመ ትውልድ የባከነ ነው» ሲሉ ተደምጠዋል።

ኢትዮጵያ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት፣ ታሪክና በዓል ያላት ሀገር በመሆኗ በየጊዜው በዩኒስኮ የሚመዘገቡ ቅርሶቿ እየጨመሩ መጥተዋል። ዘንድሮ 16 ደርሰዋል። ሆኖም ከእነዚህ ቅርሶች እንደ ሀገር ምን ያህል ተጠቅመናል የሚለው ዛሬም ምላሽ የሚያሻው ጥያቄ ነው። ከኢትዮጵያ አነስተኛ ቅርስና የተፈጥሮ መስህብ ያላቸው ሀገራት የሚያገኙት ዓመታዊ ገቢ በእጅጉ ከፍተኛ ነው።

እንደ አብነት ብንወስድ ግብጽ በዓመት ከቱሪዝም ዘርፍ እስከ 14 ቢሊዮን ዶላር ስታገኝ ሞሮኮ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ አምስት ቢሊዮን ዶላር ያፈሳሉ። ኢትዮጵያ 1ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር በማግኘት በአፍሪካ በሰባተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በዩኒስኮ በርካታ ቅርሶች በማስመዝገብ ግንባር ቀደም ለሆነችው ሀገራችን ይህ ደረጃ የሚመጥናት አይደለም።

ሆኖም ኢትዮጵያ እንደ ገናና ጥምቀት እንዲሁም ላሊበላ፣ አክሱም፣ ጎንደርና መሰል ቅርሶች በጎብኚዎች የሚወደዱ ቢሆኑም የመሠረተ ልማት አለመሟላትና ግጭትና ጦርነት ቱሪስቶችን የሚያርቁ ያልተፈቱ ማነቆዎች ናቸው። በተለይም በርካታ የቱሪስት ምስህቦች የሚገኙበት ሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በተደጋጋሚ በጦርነት አዙሪት ውስጥ መነቆጡ ኢትዮጵያ ከቱሪዝም የምታገኘው ሀብት እንዳያድግ እንቅፋት ሆኗል።

በኢትዮጵያ በቱሪዝም መስዕብነት የሚያገለግሉ ታሪክ፣ ባህልና ተፈጥሮ ናቸው። በተለይም ከታሪክ ጎብኚዎች አንጻር ትልቁ የቱሪስቶች መስዕብ በሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ያነጣጥራል። ይሁንና አካባቢው ባለፉት ጥቂት ዓመታት በጦርነት መጎዳቱ እና አሁንም ሙሉ ለሙሉ ሰላማዊ ሆኖ አለመዝለቁ ቱሪስቶች ወደ አካባቢው እንዳይመጡ አድርጓል።

በርግጥ እየተሰሩ ባሉ ሰላም የማስከበር ሥራዎች በላሊበላ የሚከበረው የገና በዓልና በጎንደር የሚከበረው የጥምቀት በዓል ሰላማዊ እንደሚሆንና በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች እንደሚታደሙበት የአማራ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ሰሞኑን ይፋ ማድረጉ መልካም ዜና ሊባል የሚችል ነው።

ሌላው ችግር ከመሠረተ ልማት ጋር የተያያዘ ነው። ቱሪዝም ሰፊ ሀብት የሚጠይቅና በሰጡት ልክ ምላሽ የሚሰጥ ዘርፍ ነው። በርካታ ሀብት ያፈሰሱ ሀገሮች በምትኩ ከቱሪዝም ዘርፉ በርካታ ሀብት ያፍሳሉ። ስለዚህም ከዘርፉ ለመጠቀም የመሠረተ ልማት ደረጃ ማሻሻል፣ ፓርኮችንና ሎጆችን ከዋና መንገድ ጋር የሚያገናኙ መጋቢ መንገዶችን መገንባትና መጠገን፣ እንዲሁም በፓርክና በእንስሳት መጠበቂያ የሚገኙ የዱር እንስሳትን አደን መከላከል፣ ቅርሶች የሚገኙበትን አካባቢ መጠበቅ ያስፈልጋል።

የሰላም እጦትና መሠረተ ልማት ችግሮች ዘወትር የሚነሳ እና ለረጅም ጊዜ የቆየ ችግር ቢሆንም ከመሠረተ ልማት ዝርጋታ ጋር በተያያዘ አሁን አሁን እየተሰሩ ያሉ ተግባራት ተስፋ ሰጪ ናቸው። በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የቱሪዝም ሀብቶችን ከመለየት፣ ከማልማትና ከመጠቀም ጋር እየተሰሩ ያሉት ሥራዎች መጪው ጊዜ ለኢትዮጵያ ቱሪዝም እንቅስቃሴ የትንሳኤ ዘመን ነው ብሎ መወሰድ ይቻላል። እስከዚያው ግን አይረሴ ጊዜያትን ለማሳለፍ ገናን በላሊበላ ጥምቀትን በጎንደር እንዲደርጉ በመጋበዝ የዛሬውን ነፅ ሃሳቤን በዚሁ ልቋጭ።

**በጅማና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶችን ሲጎበኙ ባስተላለፉት መልዕክት ‹‹ሀገሩን ያላወቀና ሀብቱን በአግባቡ ያልተጠቀመ ትውልድ የባከነ ነው›› ሲሉ ተደምጠዋል**

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ዓርብ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የከተማዋን ቮሊቦል ስፖርት ለማነቃቃትና ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ነው

ዓስማየሁ ግዛው

የቮሊቦል ስፖርት በኢትዮጵያ ተዘውታሪ ከሆኑ ስፖርቶች መካከል ይመደባል። በክለቦች፣ በቡድኖች፣ በፕሮጀክት፣ በትምህርት ቤቶችና በመኖሪያ አካባቢዎችም በስፋት ይዘወተራል። ነገር ግን ቀድሞ ስፖርቱ በስፋት ከሚዘወተርባቸው ከተሞች አንዱ በሆነው አዲስ አበባ ከወቅቶች መቀያየር ጋር ተያይዞ ተዳክሞ ቆይቷል። ይህንን ሁኔታ ለመቀየርም የከተማዋ ቮሊቦል ፌዴሬሽን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

ደማቅ ውድድሮች ይዘጋጅበት የነበረው፤ እንዲሁም ጠንካራ ተፎካካሪዎች የነበሩት ከተማው ባለፉት ጊዜያት በዓመት አንድ ጊዜ ከሚዘጋጅ ሀገር አቀፍ ውድድር በስተቀር ይሄ ነው የሚባል እንቅስቃሴ አልነበረውም። ዳግም መነቃቃት የጀመረው ከ2013 ዓ.ም ወዲህ ሲሆን፤ ለዚህም በከተማ ደረጃ ክለቦች፣ ቡድኖችና የታዳጊ ፕሮጀክቶችን ለማቋቋም በስፋት ጥረት በመደረጉ ነው። የከተማውን የቮሊቦል ስፖርት መነቃቃት ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማሳደግም ውድድሮችን ማብዛት፣ የክለቦችን ቁጥር ማሳደግ፣ ታዳጊ ስፖርተኞችን ማሰልጠንና ባለሙያዎችን በብዛት ማፍራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሆነም ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

የአዲስ አበባ ቮሊቦል ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌትሽ አስራት፤ ተወዳጅና ተዘወታሪ ከሆኑ ስፖርቶች አንዱ በሆነው የቮሊቦል ስፖርት ከሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት በፊት የነበሩ ትልልቅና ጠንካራ የከተማዋ ክለቦች በመንግሥት ለውጥ ምክንያት በመፍረሳቸው ስፖርቱ መዳከሙን ያወሳሉ። ከአራት ዓመት በፊት የተመረጠው ሥራ አስፈጻሚም ውድድሮችን በማዘጋጀት፤ እንዲሁም ሌሎች ጥረቶችን በማድረግ የተቀዛቀዘው ስፖርት እንዲያንሰራራ በመደረግ ላይ ነው።

የውድድር ዕድሎችን ከማስፋት አንጻርም የኢትዮጵያ ቮሊቦል ፕሪሚየር ሊግ ላይ የሚሳተፉ ክለቦችን ጭምር የሚያካትት ከተማ አቀፍ የዋንጫ ውድድር ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ ተካሂዷል። የክለቦች የዙር እና በከተማ ደረጃ የሚካሄዱ የተማሪዎች ውድድሮችም በተጨማሪነት ከሚደረጉ ውድድሮች መካከል ዋነኞቹ ናቸው። የዚህን ዓመት የክለቦችና የተማሪዎችን ውድድሮች ለማካሄድም ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። ከተማው ካለው የሕዝብ ብዛትና አቅም አኳያ የሚካሄዱት ውድድሮች በቂ ባይሆኑም፣ ስፖርቱ ተዳክሞ ከመቆየቱ አኳያ መሻሻሎች መኖራቸው እሙን ነው። ፌዴሬሽኑ ይህንን አጠናክሮ ለመቀጠልና ውድድሮችንም በክፍለ ከተሞችም ጭምር ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በስፖንሰር ለመሸፈን ጥረቱን እንደ ቀጠለ ነው። ለዚህም እንዲረዳ በየክፍለ ከተማው ፌዴሬሽኖች ተቋቁመው ድጋፍና ክትትል እየተደረገባቸው ሲሆን፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ ውድድሮችን ለማካሄድ በእቅድ መያዙን የጽህፈት ቤት ኃላፊው ገልጸዋል።

ከአራት ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በሚደረግ ድጋፍ ከ13 ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው አራት የታዳጊ ፕሮጀክቶች ውጤታማነትና የሚገኙበትን ሁኔታ የፌዴሬሽኑ ኮሚቴ ክትትል አድርጎ ያሉበትን ሁኔታ እየገመገመ እንደሆነም ተጠቁሟል። ሥራ አስፈጻሚውም በቦታው የቅርብ ክትትል በማድረግ የቁሳቁስ ድጋፎችን በማድረግ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በመደረጉ የተሻለ እንቅስቃሴ እየተደረገበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በክፍለ ከተማ ደረጃ የተያዙ አምስት ፕሮጀክቶች ሲኖሩ እነዚህን ለማስፋት ይሰራል። ከፕሮጀክቶቹ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስድስት ታዳጊዎች ተመልምለው በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ስልጠናቸውን በመከታተል ላይም ናቸው።

ፌዴሬሽኑ ስፖርቱን ለማነቃቃትም የክለቦችንና ቡድኖችን ቁጥር በማብዛት፤ እንዲሁም ታዳጊ ፕሮጀክቶችን ለማስቀጠል ጠንካራ ዕቅድ አውጥቶ እየሠራ ይገኛል። ለዚህም የገንዘብ አቅሙን ለማጠናከርና ድጋፎችን ለማሰባሰብ ዕቅድ ነድፎ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት የማስገባት ሥራዎችን እየሰራ ነው። በከተማው ጠንካራና በኢትዮጵያ ቮሊቦል ፕሪሚየር ሊግ የሚሳተፉ ክለቦች ሲኖሩ፤ አዲስ አበባ ፖሊስ፣ መቻል፣ ማረሚያ፣ ጌታ ዘሩ እና ብሔራዊ አልኮል ናቸው። በክፍለ ከተማ ድጋፍ የሚደረግላቸው ቡድኖች ደግሞ ለሚ ኩራና አቃቂ ቃሊቲ የሚገኙ ሲሆን፣ በዚህ ዓመት ቦሌ ክፍለ ከተማ፣ የካ እና ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቡድን ለማቋቋምና በውድድር ለመሳተፍ ምላሽ የሰጡ መሆኑንም ተጠቁሟል። ፌዴሬሽኑ ለክለቦቹ የሙያና የቴክኒክ፣ እንዲሁም ለቡድኖቹ የቁሳቁስ እገዛንም ያደርጋል። የክለቦቹንም ቁጥር ለመጨመር በ23 ተቋማት ላይ ቅስቀሳ ቢደረግም በተለያዩ ምክንያቶች ምላሽ ሳይገኝ ቀርቷል።

ለስፖርቱ ዕድገት ወሳኝ የሆነውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የአሰልጣኝነትና የዳኝነት ስልጠናዎች እየተሰጡ ሲሆን፤ በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በተጨማሪም በስፖርቱ የታየውን መነቃቃትና ዕድገት ለማስቀጠል ፌዴሬሽኑ እያከናወነ ያለውን ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አጠናክሮ እንደሚያስቀጥል የፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አረጋግጠዋል።

---

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
Ministry of Labor and Skills

## ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የማኅበረሰብ-አቀፍ ውይይት ለሥራ ባህል እድገትና ምርታማነት

እኛ ኢትዮጵያውያን በቀላሉ መልማት የሚችል ሰፊ ለም መሬት፣ መሥራት የሚችል በርካታ የሰው ኃይል እና ከራሳችን አልፎ ለሌላም የሚተርፍ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር የውኃ ሀብት ባለቤት ነን። ብዙ ዓይነት የከበሩ ማዕድናት እና ተቆጥሮ የማያልቅ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ሀብቶችም አሉን። ቢሆንም ይህን ሀብት በአግባቡ አልምቶ መጠቀም አለመቻላችን ቁጭትን የሚፈጥር ነው።

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ መንግሥት ይህንን ተቃርኖ ለመፍታት ያስችላሉ ያላቸውን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመንደፍ የመፍትሔ ርምጃዎች እየወሰደ ይገኛል። በዚህ ሂደት የሥራና ክህሎት ዘርፍ የተሰጠው ተልዕኮ የሰለጠነና የበቃ የሰው ኃይል ከማቅረብ፣ ምቹና አስተማማኝ የሥራ ዕድል ከመፍጠር እንዲሁም ጤናማና ሰላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነት እውን ከማድረግ ያለፈ ሆኖ እናገኘዋለን።

በመንግሥት ተቀርፆ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ አጠቃላይ የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገብን አልሟል። በሂደቱ ዘርፉ ሥራን፣ የሥራ ባህልን እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ጋር ተያይዞ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ኅብረተሰቡ በሙያና ሙያተኛ፤ በሥራና የሥራ ባህላችን እንዲሁም በታታሪነትና ሠርቶ መለወጥ ላይ በባለቤትነት ይመክርና ይወያይበታል። ችግሮችን እና የመፍትሔ ሃሳቦችን ከነባለቤታቸው የሚያስቀምጥበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈልጓል። ይህ ሥርዓት «የማኅበረሰብ-አቀፍ ውይይት ለሥራ ባህል እድገትና ምርታማነት! » የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል።

በየደረጃው በቋሚነት በሚካሄደው በዚህ የውይይት መድረክ አጀንዳዎች በተወያዮች በራሳቸው ይለያሉ። ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ ማኅበረሰብ ድረስ ባሉ ፅጋዎች ልክ ተጠቃሚና ምርታማ ለመሆን ተግዳሮት የሆኑ ጉዳዮችን ጨምሮ በየአካባቢያቸው ያሉና ሊፈቱ ይገባቸዋል የሚሏቸውን ችግሮችም ይለያሉ። ከችግሩ መውጫ የሚሆን መፍትሔን እና ችግሩን ሊፈታው የሚገባውን አካል ያመላክታል። ተወያዮች የራሳቸውንም ድርሻ ወስደው ለተፈፃሚነቱ በቁርጠኝነት እንዲሰሩ ይበረታታሉ።

በዚህ መልኩ የተለዩ ችግሮች በየደረጃው ባሉ መዋቅሮች እንዲፈቱ ይደረጋል። ከውይይቶቹ ሃሳብ በመነሳትና የተገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሀገራችንን የሥራ ባህል እና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል አሰራርን ይቀምራል። አዲስ የሥራ ባህል ለመገንባት፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም ምቹና ዘላቂ የሥራ ሁኔታን በመፍጠር ዜጎች በፍትሃዊነት ተጠቃሚነታቸው የሚረጋገጥበት የሥራ ምህዳር ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥርዓቶችንም ይቀርፃል።

### የውይይቱ ዓላማ

የማኅበረሰብ-አቀፍ ውይይትን እንደ ዋነኛ የችግር መፍቻ ቁልፍ በመጠቀም ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች፣

- በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብና በተቋማት ውስጥ በሥራና ምርታማነት ዙሪያ ያሉ ጠንካራ ጎኖች እንዲለዩ፣
- ከሥራ ባህልና ምርታማነት ጋር የተገናኙ ችግሮችን (የአመለካከት፣ ልማድ፣ አሠራር) በመንቀስ ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን እንዲጠቆሙ፣
- በሠራተኞችና በአሠሪዎች መካከል ያሉና አሉ ተብለው የሚታሰቡ ችግሮችንና መፍትሔዎቻቸውን እንዲመላከቱ፣
- በሥራ ባህል፣ በምርትና ምርታማነት እንዲሁም በምቹ የሥራ ሁኔታ ዙሪያ ያሉ ልዩ ልዩ ተሞክሮዎችን በማንሸራሸር ስለሥራና ምርታማነት የተሻለ ተነሳሽነትና በጎ አመለካከት እንዲዳብር ማስቻል ነው።

### የሚጠበቁ የረጅም ጊዜ ውጤቶች

- አዲስ የሥራ ባህል የተገነባበት፣ ምርትና ምርታማነት ያደገበት እና ምቹ የሥራ ሁኔታ የተፈጠረበት ማኅበረሰብ፤
- ምክንያታዊ፣ መብቱንና ግዴታውን የተረዳና የሥራ ተነሳሽነቱ ያደገ ማኅበረሰብ፤
- ግለሰቦች ከራሳቸው፣ ከቤተሰባቸው፣ ከማኅበረሰባቸው፣ ከሚያሠሩበት ከባቢ/ተቋም ጋር መተማመንና ሰላም የሰፈነበት የሥራ ምኅዳር።

### የውይይቱ ሂደት ወሰንና ምዕራፎች

ውይይቶቹ በየዞንና የወረዳ ከተሞች የሚገኙ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ታላሚ ያደረጉ ናቸው። ዓላማውም ከላይ እንደተጠቆመው በኅብረተሰብ ውስጥ ከሥራ ባህልና ከምርታማነት ጋር በተገናኘ ሁሉን-አቀፍ ችግሮችን በመነጋገር በሰለጠነ መንገድ የመፍታትን ባህል ያዳብራል። በመሆኑም ቀጣይነትና ዘለቄታነት ያለው ሂደት እንዲሆን ይጠበቃል።

ይሁንና እዛ ደረጃ ከመደረሱ አስቀድሞ በጊዜና በሥፍራ የተመጠነ ጥረት ማደረጉ ተገቢ ነው። ይህ የማኅበረሰብ-አቀፍ ውይይት ሂደት በተለያዩ ምዕራፎች ተከፍሎ ይካሄዳል። በዚህም መሠረት ውይይቶቹ እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም ድረስ በመላው ሀገሪቱ የሚካሄዱ ይካሄዳሉ። በሂደቱም 2ሺ400 የሚሆኑ በወረዳ ደረጃ የሰለጠኑ የውይይት አመቻቾች (Facilitors) የሚያስተባብሩት ከቤተሰብ ጀምሮ በጎጥ፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በክፍለ ከተማ፣ በዞን፣ በክልል እና በከተማ መስተዳድር (እንደየአካባቢው ተጨባጭ መዋቅር ሁኔታ) በየደረጃው ይካሄዳል።

በሐምሌ 2016 በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጅ መርሃ ግብር የዓመቱ የውይይት ሂደት ይደመደማል። አጠቃላይ የውይይቶቹ ምዕራፎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

**ምዕራፍ 1፡ የዝግጅት ምዕራፍ** (Preparation Phase) ይህን የማስፈጸሚያ ማኑዋል ከማሰናዳት አንስቶ ውይይቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማካሄድ የሚያግዙ አካሄዶችን መቀየስ፣ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ተገቢውን በጀት መመደብ፣ ፈጻሚ ግብረ-ኃይል ማቋቋም፣ ስለውይይቱ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጀምሮ በክልል፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ የፖለቲካና የሥራ አመራሩ ዘንድ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ አጋር አካላትን ማፈላለግና፣ ሌሎች በዚህ ምዕራፍ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው።

**ምዕራፍ 2፡ የሂደት ምዕራፍ** (Process Phase) ይህ በዝግጅት ምዕራፍ ተወጥነው የነበሩ ተግባራት ተቀናጅተው የማኅበረሰብ-አቀፍ ውይይቶቹ ከቤተሰብ ጀምሮ በጎጥ፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ክፍለ ከተማ፣ ዞን፣ ክልል ወይም እንደየ አካባቢው ተጨባጭ መዋቅር ሁኔታ በየደረጃው የሚካሄዱበት ምዕራፍ ነው።

**ምዕራፍ 3፡ የማጠናቀሪያ ምዕራፍ** (Consolidation Phase) ይህ በአንጻሩ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በማኅበረሰብ ደረጃ የተካሄዱ ውይይቶች እና በኢንዱስትሪ የሦስትዮሽ ምክክር ውጤቶቻቸው በሀገር-አቀፍ መድረክ የሚቀመርበት ምዕራፍ ሲሆን ከውይይት የተገኘው ውጤትም ሀገራዊ ስዕል እንዲሰጥ የሚያግዝ ይሆናል።

**ምዕራፍ 4፡ የማጠቃለያ ምዕራፍ** (Concluding Phase) ምንም እንኳ ውይይት በቀጣይ እንደባህል እንዲጎለበት እንደመሆኑ «ማጠቃለያ» የሚል ምዕራፍ ባይኖረውም በዓመቱ የተካሄዱ ውይይቶች የሚገመገሙበት፣ የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አካባቢዎች፣ ተቋማትና ግለሰቦች የሚበረታቱበትና የማትጊያ ሥርዓት የሚተገበርበት ምዕራፍ ነው። ይሄም የማኅበረሰብ-አቀፍ ውይይት ለሥራ ባህል እድገትና ምርታማነት ትግበራ በትክክል ውጤት እንዲያመጣ ያስችላል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ